ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 172 የካቲት 22 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

## “በውይይት፣ በንግግርና በምርጫ እያመንን ብንሄድ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም ብቻ ሳይሆን ፈጣን ልማት ይመጣል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- በውይይት፣ በንግግርና በምርጫ እያመንን ብንሄድ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም ብቻ ሳይሆን ፈጣን ልማት ማምጣት ይቻላል ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከሶማሌ፣ ከአፋር፣ ጋምቤላ፣ ሐረሪ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎችና ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከተወጣጡ ተወካዮች ጋር ውይይት አድርገዋል፡፡

“በውይይት፣ በንግግርና ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






ፎቶ፡- ገበሬ ገብሬ

## የኢትዮጵያን መጻዒ ዕድል የሚወስኑ “ሁለቱ የውሃ አካላት”

አዲሱ ገረመው

ዜና ትንታኔ

ኢትዮጵያ የቀይ ባህር ተጋሪ የነበረችና አሁንም ቢሆን በቅርብ ርቀት የምትገኝ ወሳኝ ሀገር ናት፡፡ ለዓባይ ተፋሰስም ቢሆን ከፍተኛውን ድርሻ የምታበረክት ቁልፍ ሀገር ናት፡፡ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያን ከቀይ ባህርና ከዓባይ ፖለቲካ አውጥቶ ማሰብ አይቻልም፡፡ ኢትዮጵያ ከእነዚህ የውሃ አካላት ጋር የተያያዘ ዘላቂ ፍላጎት እንዳላት የሚያሳዩ መረጃዎች በርካታ ናቸው፡፡ ለመሆኑ ሁለቱ የውሃ አካላት ከሀገሪቷ መጻዒ እድል ጋር ያላቸው ቁርኝት ምን ይመስላል?

የኢትዮጵያን መጻዒ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## በኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን አስከብራ ለመዝለቅ ያደረገችው የዲፕሎማሲ ጉዞ ተዳስሶበታል

- ለኤግዚቢሽኑ ስኬት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የዲፕሎማሲ ሳምንት ኤግዚቢሽን ኢትዮጵያ የሁለትዮሽ ግንኙነቶችን በማጠናከር ብሔራዊ ጥቅሟን አስከብራ ለመዝለቅ ያደረገችው የዲፕሎማሲ ጉዞ መዳሰስ መቻሉን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## ኢትዮጵያና ኬንያ በቀጣናው ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ተወያይተዋል

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ እና ኬንያ በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥና የኢኮኖሚ ትብብርን ማጠናከር በሚችሉበት ሁኔታ ላይ መምከራቸው ተገለጸ፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኬንያ ጉብኝትን አስመልክቶ የኢፌዴሪ መንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስቴር እና በኬንያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

የኢፌዴሪ መንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያና ኬንያ ረጅም ጊዜ የቆየ

ኢትዮጵያና ኬንያ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አምባሳደር ባጫ ደበሌ



ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር)

AfriSky PLC
ETHIOPIA


0940 80 80 80 | 0940 90 90 90 | 0911 21 72 55 | 0940 50 50 50

AMG STEEL FACTORY
ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory




## "የውሃ ማማ የተባልነው ከፍ ያለ ቦታ ላይ ስላለን እንጂ በቂ ውሃ ኖሮን አይደለም"

**- ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር**

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን የውሃ ማማ የተባልነው ከፍ ያለ ቦታ ላይ ስላለን እንጂ በቂ ውሃ ኖሮን አይደለም ሲሉ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ከዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬትና ከአብርኆት ቤተ መጻሕፍት ጋር በትብብር ያዘጋጀው ኢትዮጵያ በዓባይና በቀይ ባህር ላይ ያላትን አቋም የሚያንጸባርቅ "የሁለት ውሃዎች ዐቢይ ስትራቴጂ" የተሰኘው ታሪካዊና በአይነቱ ልዩ የሆነው መጽሐፍ በትናንትናው ዕለት ተመርቋል፡፡

ሚኒስትሩ በምረቃ መርሀ ግብሩ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ስለ ውሃ ቁጭት ከፍ ባለ ደረጃ መናገር መቻል ትልቅ ትርጉም ያለው ነው ብለዋል፡፡

በዚህም ሁልጊዜ ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት ሲባል እንደሚሰማ ጠቅሰው፤ "እኛ የውሃ ማማ የተባልነው ከፍ ያለ ቦታ ላይ ስላለን እንጂ በቂ ውሃ ኖሮን አይደለም" በማለት ገልጸዋል፡፡

ውሃ ስላለን ማማ አልተባልንም፡፡ የኢትዮጵያ ጠላቶች ይህንን ቃል ወስደው የውሃ ማማ ናቸው፤ ዝናብና ወንዝ አላቸው በማለት ለማጥቃት ይሞክራሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህ ግን ከእውነታ የራቀ ነው ብለዋል፡፡

የውሃ ማማ የሚለውን ቃል በጥንቃቄ መጠቀም እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል፡፡ ኢትዮጵያ ካላት ውሃ አብዛኛው ወደ ሌላ እንደሚሄድም ነው የገለጹት፡፡

ኢትዮጵያ የውሃ ሀብቷን እንድትጠቀም የማይፈልጉ ኃይሎች መኖራቸውን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ብዙ ጀግኖችና ታጋዮች ዓድዋ ላይ የተፈጸመውን ጀብድ ዛሬ ያለው ትውልድ መፈጸም እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ በዓባይ እና በቀይ ባሕር ላይ ያላትን አቋም የሚያንፀባርቅ የፖሊሲ ሰነድ በመጽሐፍ መልኩ መዘጋጀቱ በበርካታ ዘርፎች የጎላ ሚና እንዳለውም ተናግረዋል፡፡

መጽሐፉ በቀጣይ ኢትዮጵያ በምትቀርፃቸው ፖሊሲዎች ግብዓት ሆኖ እንደሚያገለግልም ነው ያብራሩት፡፡

ሁለቱ የውሃ ሀብቶች የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር እንዲሁም በስትራቴጂ ለመምራት የሚያስችሉ ሲሆን፣ መጽሐፉ ዘላቂና ለሀገር ህልውና ተግዳሮት የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት ታሳቢ ተደርጎ ከበርካታ ጉዳዮች አንጻር ተቃኝቶ የተዘጋጀ መሆኑ ተገልጿል።


ኢትዮጵያ በተፋሰሱ የውሃ ተጠቃሚነት ላይ ጉልህ ሚና መጫወት እንደሚገባት እንደሚዳስስ፣ የሕግና የፖሊሲ ጉዳዮችን እንደሚያነሳ፣ የቀይ ባህርና ተደራሽነቱን እንዲሁም የባህር በር ለማግኘት የተደረገው የትግል ጉዞ ከታሪክ አንጻር በስፋት እንደሚዘረዝር ተጠቅሷል።

መጽሐፉ በታሪክ፣ በፖለቲካ በሳይንስና በሌሎችም ዘርፎች ላይ ጥናትና ምርምር በሚያደርጉ ምሁራን ትልቅ ግብዓት ይሆናቸዋል ተብሎም ይጠበቃል፡፡

በምረቃ መርሀ ግብሩ ላይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መከላከያ ሠራዊት አመራሮችን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ ምሁራንና ታዋቂ ግለሰቦች ታድመዋል።

# የዓድዋ ድልን በሀገር ዕድገትና በሰላም ግንባታ ለመድገም በትጋት መሥራት ይገባል

**ታደሠ ብናልፈው**



አዲስ አበባ፡- የአሁኑ ትውልድ የዓድዋ ድልን በሀገር ዕድገትና በሰላም ግንባታ ለመድገም በትጋት መሥራት ይጠበቅበታል ሲል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ‹‹የዓድዋ የድል ቀመር ለሀገራዊ ጉዳይ በአብሮነት መቆም›› በሚል መሪ ቃል ከነዋሪዎች ጋር በትናንትናው ዕለት ውይይት አካሂዷል፡፡

በወቅቱም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ሜዴክሳ ከበደ እንደገለጹት፤ የመላ ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት አርማ የሆነውን ዓድዋን ሕብረ ብሔራዊነታችንን በማፅናት በሀገር ሁለተናዊ እድገትና በሰላም ግንባታ ላይ ለመድገም መሥራት አለብን፡፡

የዓድዋ የድል በዓል አጥንት የተከሰከሰበት፣ ደም የፈሰሰበት የነፃነት በዓል ነው ያሉት ኃላፊው፤ ይህ ከባድ መስዋዕትነት ተከፍሎ ነጻነት የተገኘበትን የድል በዓል የአሁኑ ትውልድ በሀገር ሁለተናዊ እድገትና በሰላም ግንባታ ለመድገም በትጋት መሥራት ይኖርበታል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያዊያን ከዓድዋ የጽናትና የአንድነት ትርጉም በመማር ታሪክ ሠርተን ለማለፍ በየተሰማራንበት የሙያ ዘርፍ ጠንክረን መሥራት ይጠበቅብናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ዓድዋ ኢትዮጵያዊያን ብሔር፣ ቋንቋና ሃይማኖት ሳይለያቸው በአንድነት መስዋዕትነት በመክፈል ለጥቁር ሕዝቦች ነፃነትን ያሳዩበት ትልቅ የድል በዓል ነው ብለዋል፤ አሁንም ከዚህ የድል በዓል ተምረን ልዩነታችንን አቻችለን ሀገርን ለማሳደግ በትኩረት መሥራት አለብን ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የዓድዋን በዓል ስናከብር ሁሉን በአካተተ መልኩ መሆን አለበት ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ የሀገርን ሰላም ማስጠበቅና ድህነትን ማሸነፍ ይኖርብናል ሲሉ አመልክተዋል፡፡

በውይይቱ ስለዓድዋ ጥናታዊ ጹሑፍ ያቀረቡት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ሕዝብ አደረጃጀት ዘርፍ ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍሬህይወት በለጠ በበኩላቸው፤ ዓድዋ ህብረ ብሔራዊነት የታየበት የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት በዓል ነው፤ ይህን ትልቅ የድል በዓል ሀገርን በማሳደግ ልንደግመው ይገባል ነው ያሉት፡፡

የዓድዋ ድል መታሰቢያ በዓል ከግል ፍላጎት ይልቅ የሀገር ፍቅር ጎልቶ የታየበት፤ ከልዩነት ይልቅ አንድነት የፀናበት የነፃነት በዓል ነውም ብለዋል፡፡

ሃይማኖትንና ፖለቲካን ለፅንፈኝነት አስተሳሰብ ሽፋን በማድረግ ሀገርን ለማፍረስ የሚሰሩ ኃይሎች የሴራ



ካባቸውን አውልቆ ማሳየትና ሰላምን ማስፈን ይገባል ብለዋል፤ በአንድነት በመቆም ታላቋን ኢትዮጵያ ማስቀጠል እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡


ዓድዋ መስዋእትነት የተከፈለበትና ዛሬ በነፃነት ለመኖር ያስቻለን ትልቅ የድል በዓል ነው ሲሉ በውይይቱ የተሳተፉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ተናግረዋል፡፡

ነዋሪዎች የዓድዋን የድል በዓል በሀገር እድገትና በሰላም ግንባታ ለመድገም በአንድነት እንሠራለን ብለዋል፡፡

# ካፒታል ገበያውን ከወንጀል ድርጊት ለማራቅ በቴክኖሎጂ የመደገፍ ሥራ እየተሠራ ነው

**- ባለስልጣኑ ከሰባት ተቋማት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ**

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- ካፒታል ገበያውን ከወንጀል ድርጊት ለማራቅ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግና በተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ለመዘርጋት እየተሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን አስታወቀ።

ባለስልጣኑ ታዓማኒነቱንና የቴክኖሎጂ አቅሙን ለማሳደግ ከሰባት ተቋማት ጋር የመግባቢያ ሰነድ በትናንትናው ዕለት ተፈራርሟል።

የባልስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ታዬ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ካፒታል ገበያውን ከወንጀል ድርጊት ለማጽዳትና በቴክኖሎጂ ለመደገፍ እየተሠራ ነው።

ካፒታል ገበያው አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የቅንጅት ሥራ ያስፈልገዋል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በቀጣይነት ተግባራዊ የሚደረጉ የካፒታል ገበያ ሥራዎችን በቴክኖሎጂ ለመደገፍና ከወንጀል ድርጊቶች የጸዳ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ገበያው ላይ ተዓማኒነት በጎደለው መልኩ ሼር የሚሸጡ አካላት እንደሚስተዋሉ ገልጸው፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ወደ ሕጋዊ ሥርዓት ለማስገባት እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

የካፒታል ገበያው ተዓማኒነት በተረጋገጠ መልኩ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና አዋጁ በሚፈቅደው መሠረት የሼር ካምፓኒ በማቋቋም ድርጅቶችን ማስፋፋትና ሼሮችን መሸጥ የሚያስችል ማዕቀፍ ተዘርግቷል ብለዋል።

በቀጣይ የኢትዮ ቴሌኮም 10 በመቶ የሚሆነው ሼር ወደ ገበያ ሲወጣ የግብይት ሥርዓቱን በቅንጅት በመሆን ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን የካፒታል ገበያውን ተዓማኒነትና የቴክኖሎጂ አቅሙን ለማሳደግ የሚያግዝ ሁለት ስምምነቶችን ከሰባት ተቋማት ጋር በትናንትናው ዕለት ተፈራርሟል።

የካፒታል ገበያ መሠረተ ልማቶችን ለማጠናከር፣ ግልጽነትን ለማጎልበት፣ የቴክኖሎጂ አቅምን ለማሳደግ እና ካፒታል ገበያን ከወንጀል ድርጊቶች የጸዳ ለማድረግ ባለስልጣኑ ከሰባት ተቋማት ጋር ሁለት የመግባቢያ ስምምነቶችን መፈራረሙን አስታውቀዋል።

የመግባቢያ ስምምነቱ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ተዓማኒነት ግብረ ኃይል የትብብርና የቅንጅት መግባቢያ እና የካፒታል ገበያ ባለስልጣን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ የተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ተዓማኒነት ግብረ ኃይል የትብብርና የቅንጅት የመግባቢያ ስምምነት የመጀመሪያው ስምምነት ሲሆን፤ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ከፍትህ ሚኒስቴር፣ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና ከፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ጋር ተፈራርሟል።

"የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ታአማኒነት ግብረ ኃይል ስምምነት ዓላማ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያን ሕጋዊና ከወንጀል ድርጊቶች የፀዳ ለማድረግ እንዲሁም በተቋማቱ መካከል ቋሚና ቅንጅታዊ አሠራር ለመዘርጋት መሆኑን ተናግረዋል።

ግብረ ኃይሉ በሕገወጥ የአክሲዮን አቅርቦት ላይ የተሰማሩ እና ለበርካታ ኢንቬስተሮች የገንዘብ ማጣት ምክንያት የሆኑ አክሲዮን ሻጮችን በመለየት ለፍርድ የማቅረብ ኃላፊነት እንዳለበትም አመልክተዋል።

ሁለተኛው ስምምነት የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣንን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ የተደረገ የትብብር መግባቢያ ስምምነት ሲሆን፤ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ፣ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ መታወቂያ አገልግሎት ተፈራርመውታል።

ስምምነቱ ከሳይበር ደህንነት ጋር የተያያዙ የቴክኖሎጂ ድጋፎችን ለማድረግ፣ የመስሪያ ቤቱን ገበያ እና የኢንቬስተሮችን ደህንነት ለመጠበቅ ዓላማ ያደረገ መሆኑን ገልጸው፤ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን በንቃት በመከታተል የቁጥጥር ማዕቀፉን ለማሳደግ በትብብር ለመሥራት ነው ብለዋል።

የፍትሕ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ባለስልጣኑ በካፒታል ገበያው ላይ ከሚያደርገው አስተዳደራዊ ክትትልና ቁጥጥር አልፎ የሚፈጸሙ የሕግ ጥሰቶችን አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት በመመርመር ተጠያቂ የማድረግ ሥራ ይከናወናል።

በካፒታል ገበያው የሚሳተፉ አካላትን እምነት እንዳይሸረሸር፣ ሕግና ሥርዓት እንዲከበር ለማድረግ በየጊዜው መረጃን በመለዋወጥ በቅንጅት እንደሚሠሩ ገልጸው፤ ሕግና ሥርዓትን አክብረው የማይሠሩ አካላትን በሕግ ተጠያቂ እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል።

የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና (ኢ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ለካፒታል ገበያ ልማት የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት፣ ዳታዎችን በመሰብሰብ እና በመተንተን እንዲሁም ስልጠና በመስጠት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ደኅንነቱ የተጠበቀ የካፒታል ገበያ ሥርዓት ዕውን ለማድረግ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂ ትልቅ ሚና ያለው በመሆኑ በትብብር እንሠራለን ብለዋል።

ስምምነቱን የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ታዬ (ዶ/ር) እና የሰባቱም የተቋም ኃላፊዎች ተፈራርመውታል።

# ኢትዮጵያ የሚመጥናትን ተቀባይነት እንድታገኝ መሥራት ይገባል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ድልን ከማክበር ባለፈ ኢትዮጵያ የሚመጥናት አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት እንዲኖራት መሥራት ይገባል ሲሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ገለጹ፡፡

ዓድዋ የመደመር ተምሳሌታዊ አርማ በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት የፓናል ውይይት በተካሄደበት ወቅት አምባሳደር ዲና ሙፍቲ እንደገለጹት፤ የጥንት አባቶች የራሳቸውን ታሪክ እንደሠሩት ሁሉ የኛስ ዓድዋ ምንድነው የሚለውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መሥራት ይገባል።

አባቶቻችን የሠሩትን ታሪክ በመዘከር መሆኑ ሊጠናከር የሚገባው ትልቅ ተግባር ነው ያሉት አምባሳደር ዲና፤ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና ነጻነት ማስከበር ብሎም ኢትዮጵያ የሚመጥናትን አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስፍራ እንዲኖራት መሥራት ይህ ትውልድ ሊታገልለት የሚገባው ዓድዋው ነው ብለዋል።

ወጣቱ ከድህነት፣ ከመሐይምነትና ከኋላ ቀርነት መውጣት በሚያስችሉት በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በትኩረት መሥራት ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በዓድዋ ጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያውያን የባህል፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት ልዩነት ቢኖራቸውም ይህን ልዩነት ወደ ጎን በመተው አንድ ለምታደርጋቸው ሀገራቸው መዋጋታቸውን አስታውሰዋል።


የአሁኑ ትውልድም ልዩነቱን ወደ ጎን በመተው በትብብርና በአንድነት በመሥራት ሀገሩን ሰላማዊና የለማች በማድረግ ታሪክ መጻፍ እንደሚኖርበት ተናግረዋል፡፡

ለትውልዱ ዓድዋን በማስተማር ይበልጥ አንድነቱን እንዲያጠነክር፣ ለልማት እንዲነሳሳና፣ ሀገሩን በመጠበቅ ስንቅ እንዲይዝ ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከዓድዋ ድል በኋላም በየዘመኑ በዲፕሎማሲውና በሌሎች ዘርፎች በርካታ ተምሳሌታዊ ታሪኮች መፈጸሟን አውስተው፤ የተለያዩ ሃሳቦችን ይዘው የነበሩትን የካዛባላንካና የሞኖሮቢያ ቡድኖችን ሃሳብ በማስታረቅ ለአፍሪካ ኅብረት ድርጅት ምስረታ ትልቅ ሚና መጫወቷንና ከራሷ ባለፈም የኮሪያ የሩዋንዳ ፣የኮንጎ ፣የብሩንዲ ፣የሱዳን ፣የሶማሊያና ሌሎች ሀገራት ሰላም በማስጠበቅ አስተዋጽኦ ያበረከተች ሀገር መሆኗን አንስተዋል፡፡

የጥቁር ሕዝቦች ኢትዮጵያን የነፃነት ምሳሌ አድርገው እንደሚመለከቱ የገለጹት አምባሳደሩ፤ ዓድዋን በዓለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ የገቢ ምንጭ ማድረግ እንደሚቻል ጠቅሰዋል።

በታሪክ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር፣ የተሰሩ መልካም ነገሮችን ማስቀጠል እንዲሁም ዓድዋን ከሀገር ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንና የመንግሥት አካላት በዓሉን በተጠናከረ ሁኔታ እንዲያከብሩት ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።



አምባሳደር ዲና ሙፍቲ



# ስብራቶቻችንን የምንጠግነው
## ትውልድ ላይ በመሥራት ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- እንደ ሀገር የገጠሙ ስብራቶች ለመጠገን ትውልድ ላይ በትኩረት መሥራት እንደሚገባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራንን ትናንት አስመርቋል፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በመርሀ ግብሩ ላይ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ እንደ ሀገር የገጠሙ ስብራቶችን ለመጠገን ትውልድ ላይ በትኩረት መሥራት ይገባል፡፡

ከዚህ ቀደም ትውልድ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ በቂ ሥራ አለመሠራቱ ዛሬ ላለንበት ክፍተትና ስብራት ዳርጎናል ያሉት ከንቲባዋ፤ እያጋጠመ ያለውን የትምህርት ጥራትና ውጤት ትውልድ ላይ ያለመሠራቱ አንዱ ማሳያ ነው ብለዋል።

ትውልድ ላይ ክፍተት በመኖሩ የሀገር ፍቅር እየላላ መምጣቱን ጠቅሰው፤ በተለይም ተባብሮ ከመሥራት ይልቅ በማይሆኑ ጉዳዮች ጊዜን ማባከኖች እንደሚስተዋሉ ገልጸዋል፡፡

መዲናዋ ክፍተቶችን በማስተካከል ሕፃናትን ለማሳደግ ከአፍሪካ ምርጧ ከተማ ለመሆን እየሠራች እንደምትገኝ የገለጹት ከንቲባ አዳነች፤ ይህ ሊሳካ የሚችለው ትውልድ ላይ በተለይም በጨቅላ ሕፃናት ላይ ውጤታማ ሥራ መሥራት ሲቻል ነው ብለዋል፡፡

ለእቅዱ ውጤታማነት የመምህራን ኃላፊነት ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድ ጠቅሰው፤ ከተማ አስተዳደሩ ይህን ታሳቢ በማድረግ ለመምህራን ስልጠና ለሥራ ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

መምህራን ኃላፊነት ተሰምቷቸው የተማሩትን መተግበር እንደሚገባቸው የገለጹት ከንቲባዋ፤ መምህራን ልጆችን ውጤታማ ለማድረግ ኃላፊነታቸውን በጥንቃቄ ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ በበኩላቸው፤ ከተማ አስተዳደሩ በቀዳማይ ልጅነት መርሀ ግብር «የነገ ተስፋ ሕፃናት ለአዲስ አበባ» በሚል መሪ ቃል እየተገበረው የሚገኝ ሰው ተኮር ሥራ ነው ብለዋል።

ለቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራን የተሰጠው ስልጠና ዋነኛ አላማው ከአንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን በላይ ሕፃናት ሁለንተናዊ እድገታቸው እንዲረጋገጥ መሆኑን ጠቅሰው፤ ልጆች በእድገት ክትትል ሥርዓት ውስጥ እንዲያድጉ ማብቃት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የቀዳማይ እንክብካቤና ትምህርት ከቅድመ ወሊድ እስከ ስድስት ዓመት ያለውን ጊዜ የሚያካትት መሆኑን በመግለጽ ፈጣን እድገት፣ ለሕፃናት ደኅንነት፣ በህይወት ለመኖር፣ለእድገታቸውና ጤንነታቸውን ጨምሮ ለመማርና ለመብታቸው መረጋገጥ መሰረት የሚጣልበት ወሳኝ ጊዜ ነው ብለዋል።

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ስልጠና ሕፃናትን ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማዘጋጀት የሚሰጥ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለእድሜ ዘመን ትምህርት አካላዊ፤ ማህበራዊና ስሜታዊ እድገቶቻቸውን በማዳበርና ኃላፊነት የሚሰማቸው ሕፃናት ለመፍጠር ታስቦ የሚተገበር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ትምህርቱ ሕፃናት ባህላቸውን እንዲያውቁ፣ እሴታቸውን እንዲገነዘቡ፣ እውቀትና ክህሎት እንዲጨብጡ የሚያስችል ነው ያሉት ዶክተር ዘላለም፤ ስልጠናውን በጨዋታ የማስተማር ዘዴ በመጠቀም የሚሰጥ ነው ብለዋል፡፡

# የፋርማሲ አገልግሎት
## ደረጃ ተግባራዊ ሊደረግ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**




አዲስ አበባ፡- የመድኃኒት ቁጥጥር ሥርዓቱን ለማሳደግ የፋርማሲ አገልግሎት ስ ታ ን ዳ ር ድ ተዘጋጅቶ በደረጃዎች ኢ ን ስ ቲ ት ዩ ት መ ጽ ደ ቁ ን የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን አስታወቀ።

ባ ለ ስ ል ጣ ኑ ከክልል ጤና ተቆጣጣሪ አካላት ጋር የ2016 በጀት ዓመት የስድስት ወራት የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ ትናንት አካሂዷል።

በመድረኩ የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ሄራን ገርባ እንደገለጹት፤ የመድኃኒት ቁጥጥር ሥርዓቱን ለማሳደግ የፋርማሲ አገልግሎት ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ በደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጸድቋል።

የፋርማሲ አገልግሎት ስታንዳርዱን ወደ ተግባር ለማስገባት ሰፊ ሥራ ይጠይቃል ያሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ ይህም በቅርቡ ተግባራዊ ለማድረግ ከጤና ሚኒስቴር፣ ከክልል ጤና ተቆጣጣሪዎች፣ ከከተማ አስተዳደሮች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር እንደሚሠራ ተናግረዋል።

ለሀገር ውስጥ መድኃኒት አምራቾች ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀታቸውን ጠቁመው፤ ባለፉት ስድስት ወራት በምግብ ላቦራቶሪና በ2 የምግብ ዘርፎች እውቅና የማግኘት ሥራ ተሠርቷል። ከዚህም ባለፈ በመድኃኒት ቁጥጥር ላይ ሰፊ ሥራ የተሰራ ሲሆን፤ በዚህም በተቋሙ አደረጃጀት እና ቁጥጥር ሥራ ላይ በርካታ ውጤት መገኘቱን ገልጸዋል።

በመድረኩ የተቋሙን የስድስት ወር አፈጻጸም ያቀረቡት አቶ ክንዳለም በረካው በበኩላቸው፤ ባለስልጣኑ የቁጥጥር፣ የፈቃድና የጥራት ምርመራዎችን ያደርጋል። ይህም በምግብና መድኃኒት ላይ የሚከናወን ነው። ባለስልጣኑ 481 ለሚደርሱ ተቋማት የመድኃኒት ገበያ ፈቃድ ሰጥቷል ብለዋል።

በቁጥጥር ሥራው በባለስልጣኑ እውቅና ያልተሰጣቸው፣ የብቃት ማረጋገጫ ያላደሱ፣ ሕጋዊ ደረሰኝ የሌላቸው እና በንግድ ፈቃድ ብቻ ምግብና መድኃኒት ሲሸጡ የነበሩ ነጋዴዎች ተገኝተዋል ያሉት አቶ ክንዳለም፤ ለእነዚህም ተቋማት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ የእገዳ እና የፈቃድ ስረዛ ርምጃ መወሰዱን ተናግረዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት ለ428 ተቋማት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ 118 ተቋማትን ደግሞ የማሸግ እንዲሁም 36 ተቋማትን ፈቃድ የመሰረዝ ሥራ ተሠርቷል ያሉት አቶ ክንዳለም፤ 86 ተቋማት ደግሞ እንዲታገዱ መደረጉን ገልጸዋል። በዚህም ከ207 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ ምርቶች እንዲወገዱ ተደርጓል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን የቁጥጥር ዘርፉን የ2016 በጀት ዓመት ግማሽ ዓመት የለውጥና የመልካም አስተዳደር ጉዳይ አፈፃፀምን ያቀረቡት ደግሞ አቶ ወየሳ ወቀሬ ሲሆኑ፤ ለባለስልጣኑ በ8182 ነፃ የስልክ መስመር ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ ጥቆማዎች ማቅረባቸውን ተናግረዋል።

በመድረኩ ከጤና ሚኒስቴር፣ ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን አመራሮች፣ ከክልል ጤና ተቆጣጣሪ አካላት እና ከUSP/PQM plus የተውጣጡ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሁለት ውሃዎች አብይ ስትራቴጂ ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን ለማስጠበቅ ቁልፍ እይታ ነው

ሀገራችን የቀይ ባህር ተጋሪ የነበረችና አሁንም ቢሆን በቅርብ ርቀት የምትገኝ ወሳኝ ሀገር ናት። ለዓባይ ተፋሰስም ከፍተኛውን ድርሻ የምታበረክት ቁልፍ ሀገር ናት። ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያን ከቀይ ባህርና ከዓባይ ፖለቲካ አውጥቶ ማሰብ የሚቻል አይደለም። ከዚህም ባለፈ ከነዚህ የውሃ አካላት ጋር የተያያዘ ዘላቂ ፍላጎት አላት። የውሃ አካላቱ ከሀገሪቱ ደኅንነትና ህልውና ጋር ያላቸው ቁርኝትም ከፍ ያለ ነው።

አሁን ካለችበት ኋላቀርነት እና ድህነት በልማት ወደ ብልጽግና ለመጓዝ ለጀመረችው ሀገራዊ የልማት ንቅናቄ ስኬትም ፤ የእነዚህ የውሃ አካላት አስፈላጊነት መተኪያ የሌለው ነው። ለበለጸገች ሀገር ግንባታ ዋነኛ አቅሞች መሆናቸውም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

አሁንም ላይ ወደ ባህር ተጋሪነት ማማተራችን፤ በቀይ ባህር ቀጣና ላይ የነበረንን ሥፍራ ለመመለስ ሆነ በአዲስ መልክ በቀጣናው ቁልፍ ተዋንያን በመሆን የሀገራችንን ደኅንነት በተሻለ መልኩ ለማረጋገጥ እንደሚረዳን ይታመናል። ወደ ዓባይ ተፋሰስ ከሚገባው ውሃ የተወሰነውን መጠቀም ካልቻልንም አሁን ላይ እየተፈታተነን ያለው ድህነት እየከፋ ሊሄድና ወደ ቀውስ ሊያመራ እንደሚችል እንዲሁ ።

እየጨመረ ያለው የሕዝብ ቁጥር፣ የከተሜነት መስፋፋት፣ የግብርና ምርቶች ፍላጎት መጨመርና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻችን የውሃ ሀብቶቻችንን በይበልጥ እንድንጠቀም ያስገድዱናል። ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣው የኃይል ፍላጎትም ሊሟላ የሚችለው ወደ ዓባይ ተፋሰስ የሚቀላቀሉ የውሃ ሀብቶቻችንን ባግባቡ መጠቀም ስንችል ነው ።

እነዚህ የውሃ አካላትን ለመጠቀም የምናደርጋቸው ጥረቶች ተጨማሪ የስጋት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታመናል ።እስካሁን የመጣንባቸው መንገዶችና ይህንኑ እውነታ በተጨባጭ የሚያመላክቱ ናቸው።በቀጣይም ተመሳሳይ ተግዳሮቶች እንደሚያጋጥሙን ብዙም አጠያያቂ አይሆንም።

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያ ህልውናም ሆነ ደኅንነት ከሁለት የውሃ አካላት / ከቀይ ባህር እና ከዓባይ ተፋሰስ / ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። የውሃ አካላቱ ለመቆጣጠር የሚደረገው ትግል ከቀደሙት ዘመናት ጀምሮ ዛሬም የቀጠለ ነው፡ እነዚህን የውሃ አካላት መቆጣጠር የሚፈልግ የትኛውም የውሃው ተጋሪ ሀገርም ሆነ ሌላ በየወቅቱ የሚነሳ ሉዓላዊና ቀጣናዊ ኃያል ሀገር በአንድም ሆነ በሌላ በኢትዮጵያ ላይ የደኅንነት ጫና ማሳደሩ የማይቀር ነው።

የውሃ አካላቱ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ የመሆናቸውን ያህል ለሌሎች የውሃ ተጋሪዎችም ሆነ ሌላ ፍላጎት ላላቸው ሀገራት ጠቃሚ የውሃ አካላት ናቸው። ቀይ ባህር በዓለም ላይ የንግድ ኮሪደር ከሆኑ የውሃ አካላት መካከል አንዱ ነው፤ ለውሃው ተጋሪ ሀገራት ደግሞ ከኢኮኖሚ በዘለለ በርካታ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞች አሉት።

የዓባይ ተፋሰስን ኢትዮጵያ የምትፈልገውን ያህል ሌሎች የተፋሰሱ ሀገራት በተለይም የታችኞቹ የተፋሰስ ሀገራት በእጅጉ ይፈልጉታል። ከውሃ አካላቱ የሚገኘው ጥቅም በርካታ ከመሆኑ የተነሣ ተዋናዮችም በርከት ያሉና የተለያየ የኃይል አቅም ያላቸው ናቸው። የውሃ አካላቱ ተጋሪ ሆነውም ሆነ በርቀት ላይ የሚገኙ ሀገራት መብዛታቸው ለተጠቃሚነት የሚደረገውን ትግል ከባድና ውስብስብ ያደርገዋል። በታሪክ እንደታየውም እነዚህ የውሃ አካላት የግጭትና የትግል መንስኤ ሆነው አገልግለዋል።

ሀገራችን በእነዚህ የውሃ አካላት ምክንያት ከጥንት ጀምሮ ሥጋት እያስተናገድን ነበር ፤ አሁንም በተመሳሳይ ሥጋት ውስጥ ነች ፤ወደፊትም ውሃዎቹን ታሳቢ ያደረጉ ስጋቶች ከፊታችን ይጠብቁናል፣ ይህንን ሀገራዊ ተጨባጭ እውነታ በስኬት ለመሻገር ሥጋታችንን እየቀነስንና ጥቅማችንን እያሳካን መሄድ የሚያስችል ስትራቴጂክ እይታ ያስፈልገናል።

አሁን ያለንበት ተጨባጭ እውነታ ሆነ ወደ ፊት ሊያጋጥሙን ከሚችሉ ችግሮች አንጻር ያለን አማራጭ እጆቻችንን አጣጥፎ አርፎ መቀመጥ ሳይሆን፣ የትኛውንም አይነት ችግር እንደየባህሪው እየተጋፈጥን ጥቅሞቻችንን እያስከበርን መሄድ ብቻ ነው ።ለዚህ ደግሞ እንደ ሀገር ሁለንተናዊ ዝግጁነት ያስፈልገናል።

ከዚህ ተጨባጭ እውነታ አንጻር ትናንት ለህትመት የበቃው የሁለት ውሃዎች አብይ ስትራቴጂ ሰነድ፤ ከውሃ አካላት ጋር በተያያዘ ሀገራችንን እየገጠማት ያለውን ዘላቂ የህልውና እና የደኅንነት ሥጋት በማመላከት ጥቅሞቿን ልታሳካ የምትችልባቸውን የመፍትሔ መንገዶች ማመላከት የሚያስችል ነው።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዓድዋና ኒኮላይ እስቴፓኖቪች ሌዎንቴቭ

ሰላማዊት ውቤ

አሜሪካዊው ፀሐፊ ማርክ ትዌይን፤ «ታሪክ ራሱን አይደግምም፤ የእገሌ ዘመን፣ የምንትሴ ዘመን ከሚለው መመሳሰል ውጪ ነው» ይላል። እርግጥ ነው ፀረ ቅኝ አገዛዝ ጦርነት በተለያዩ አካባቢዎችና ሀገራት ተደርጓል። በእስያ፣ በላቲን አሜሪካ፣ በአፍሪካ ለነፃነታቸው ለረጅም ዘመናት የታገሉና ድልም የተቀዳጁ አሉ፤ የአድዋው ጦርነት ግን በተደረገበት የታሪክ የዘመን ነቁጥና ሥፍራ ሲታይ እጅግ አንፀባራቂና ቀዳሚ ቦታ ያለው ነው። የዛሬው ጽሑፉ ማጠንጠኛም ከዚሁ የዓድዋ ገድል ጋር በቅርብ የተገናኘ አንድ ሩሲያዊን ማስታወስ የፈለገ ነው፡፡

ኒኮላይ እስቴፓኖቪች ሊዎንቴቭ ይባላል፤ ይህ ሰው የዓድዋ ጦርነት ከመጀመሩ ጥቂት ጊዜያት በፊት ከአፄ ምኒልክ ጋር በቅርብ የተዋወቀ ነው፤ ሰውየው የሩሲያ የሚሊታሪ መኮንን የነበረ ሲሆን፤ በተለያዩ የዓለም አካባቢዎች የተጓዘ ሀገር አሳሽና የጂኦግራፊ ሚሲዮን አባልም ሆኖ ሀገሩን ሩሲያን አገልግሏል።

በ1887 ዓ.ም ከጥቂት ረዳቶቹና ከበጎ ፈቃድ ተጓዦች ጋር በመሆን ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል፤ አመጣጡም በኦፊሴላዊ መንገድ የሩሲያ መንግሥትን ተልዕኮ በመያዝ በጊዜው ለነበሩት ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ለማድረስ ነበር፡፡አፄ ምኒልክ ከዚህ ሰው ጋር ጥሩ ወዳጅነትና መቀራረብ እንደፈጠሩና አንዳንድ ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ጉዳዮች እንደፈፀሙ በታሪክ ተፅፎ ይገኛል፤ ወቅቱ በአውሮፓውያኑ የቅኝ ግዛት እሽቅድድም ወደኋላ የዘገየችው ኢጣሊያም ኢትዮጵያን ለመያዝ ዝግጅቷን ሁሉ ጨርሳ ትንኮሳዎችን እምታደርግበት ሰዓት መሆኑም ይታወሳል፡፡

ሊዎንቴቭ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የነበረውን ቆይታ ጨርሶ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ምኒልክ 30ሺ ጠመንጃ፣ ከ5 ሚሊዮን በላይ አረርና ጥይት፣ 42 ያህል የተራራ ላይ መድፎች እንዲያመጣላቸው ከአደራ ጋር ለመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ኒኮላ የተጻፈ ደብዳቤ አስይዘው እንደ ላኩት፤ አፄ ምኒልክ ተልዕኮውን ከፈፀመ በኋላም ለዚህ የችግር ቀን ወዳጃቸው ለሆነ ሰው የማዕረግ ሽልማትም እንደሰጡት በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል።ይህም ሆኖ ግን የተጠበቀው ወታደራዊ እርዳታ መድረስ የቻለው የዓድዋ ውጊያ ከተፈፀመ ከሦስት ወራት በኋላ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ይናገራሉ፡፡

አፄ ምኒልክ የላኩት ደብዳቤ ሙሉ ቃል ይህን ይመስል ነበር ፦

"ይድረስ ከክቡር ወልዑል ቄሣር ከመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ኒኮላ... ሰላምና ጤና ለርስዎ ይሁን ። ከርስዎ ዘንድ የተላኩ መነኩሴና መኳንንቶች በደህና ደረሱ። እኛም በክብርና በደስታ ተቀበልናቸው፡፡ የክቡር አባትዎን ሞት ሰምተን እጅግ አዝነን ነበር። እርስዎ በእግዚአብሔር ፈቃድ በሕዝብዎ መውደድ ባባትዎ ዙፋን መቀመጥዎን ሰምተን በጣም ደስ ብሎናል።

"ግዛትዎና ዕውቀትዎ እየበዛ እየተረፈ እንዲሔድ እጅግ ተስፋ አለን። ያባትዎን የጥንት ፍቅርና ወዳጅነት አለመርሳታችንን ለማስታወቅ ኃዘንዎና ኃዘናችን አንድ ዘንድ እንዲተባበር ብለን ከንጉሠ ነገሥት (እስክንድር) መቃብር ላይ የሚደረግ የኢትዮጵያ ዘውድ ሰደናል። ከዘውዱም ጋራ የታመኑ ሰዎቻችንን ሰደናል፡፡

"ዳግመኛም የክርስቲያን ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ወንድሞቻችሁ መሆናችንን የሚያስረዳ ፍቅራችንንም የሚያሳይዎ ወንጌልና የወርቅ መስቀል ልከናል። እርስዎም በክቡር (አክብረው) እንዲቀበሉን ተስፋ አለን። ክቡር አባትዎ ዊክቶር (ቪክቶር) ማሽኮፍን ወደኛ የላኩ ጊዜ የጻፉልኝን የፍቅር ደብዳቤያቸውን ቃል እርስዎም እንዳይረሱ እናውቃለን።

"ዕድሜዎን እንዲያራዝም መንግሥትዎን የእርቅ የሰላም አድርጎ እንዲያሰነብትዎ መልካም አሳብዎን ሁሉ እንዲፈጽምልዎ ይልቁንም ክርስቲያን በመርዳትዎ እንዲጠብቅዎ ልዑል እግዚአብሔርን እለምናለሁ። በሚያዝያ በ22 ቀን በአዲስ አበባ ከተማ በ1887 ዓ.ም ተጻፈ."

ንጉሰ ነገሥቱ ደብዳቤያቸው እንደሚያመለክተው፤ የጣሊያኖች ትንኮሳ ወደ ለየለት ጦርነት መግባቱ እንደማቀር፣ ለዚህ የሚሆን በቂ ዝግጅት ማድረግ እንዳለባቸው ፤ በሊዎንቴቭ በኩል በሁለቱ ሀገራት መካከል የተጀመረው ግንኙነት ይህንኑ ፍላጎታቸውን ተጨባጭ ለማድረግ እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ እንደተጠቀሙበት የሚጠቁም ጭምር ነው።

ሁኔታው ንጉሰ ነገሥቱ እንዳሰቡት ባይሆንም፤ ኢትዮጵያውን ለነጻነታቸውና ለፍትህ ካላቸው ቀናኢነት የተነሳ ወራሪውን የጣሊያን ጦር በዓድዋ ድል አድርገዋል። ይህ ለአንድ ዓላማ በአንድነት የመቆም ፤ ሀገርን ያለማስደፈር የተጋድሎ ታሪክ ዛሬ የመላው አፍሪካ (ፓን- አፍሪካዊነት) ምልክት ሆኗል፤ የአይበገሬነትና የአንድነት ትግል ተምሳሌት በመሆንም ይቀጥላል፤ ኢትዮጵያ በዓደዋ ድል ማድረጓን ተከትሎ ዙሪያዋን የከበቧት ኢምፔሪያሊስቶችና ቅኝ ገዥዎች አደብ እንዲገዙ አድርጓል፡፡

የኢትዮጵያና የሩሲያ ግንኙነት ብዙ ታሪካዊ አጋጣሚዎችን የሚጠቅስና መልከ ብዙ ቢሆንም በሊዎንቴቭ የተጀመረው ወዳጅነት ግን እንደ ዓድዋው ድል ሁሉ ዘመን ተሻጋሪ ሆኗል፤ የኋላ ኋላ ተጠናክሮ በርከት ላሉና በሁለቱ ሀገራት በተግባር ለተተረጎሙ ክንዋኔዎች ምክንያትም ሆኗል።

ከጊዜ በኋላ ተጠናክሮ ለተከፈተው የደጃች ባልቻ ሆስፒታል ይህኛው አጋጣሚ እርሾ ሆኖ እንዳገለገለ አይካድም፤ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጥቅምት 16 ቀን 1950 ዓ.ም የደጃች ባልቻ ሆስፒታል ምሥረታ 10ኛ ዓመት በዓል ላይ ሲናገሩ፤ የሩሲያ መንግሥት ለዜጎቻቸው ጤንነትና ደህንነት የሚያግዙ ተግባራትን በመፈፀሙ እጅጉን መደሰታቸውን ጠቅሰው ምስጋና አቅርበዋል፡፡

ሩሲያ ከዚያም በኋላ በተለያዩ የታሪክ ምዕራፎች ውስጥ ኢትዮጵያውያን በፈተናዎች ውስጥ በሆኑባቸው ወቅቶች የክፉ ቀን ወዳጅነቷን በተጨባጭ አስመስክራለች። በየዓለም አቀፉ መድረክ ሳይቀር ለኢትዮጵያ ያላትን አጋርነት በተጨባጭ አሳይታለች፡፡

ይህ በኒሎላይ እስቴፓኖቪች ሊዎንቴቭ የተጀመረው ምንም ዓይነት ቅኝ ግዛታዊና ኢምፔሪያሊስታዊ ፍላጎትና ዓላማ ያልነበረው የኢትዮጵያና የሩሲያ ግንኙነት በሌሎችም መስኮች በተደረጉ ትብብሮች ተደግሟል፤ ሩሲያኖች (ምስኮቦች) በባህርዳር የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ በአሰብ የነዳጅ ማጣሪያ ድጋፍና ትብብር አድርገዋል፡፡ ኢትዮጵያ በሶማሊያ በተወረረችም ጊዜ በወታደራዊ መስክ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቆሙ አስችሏል፡፡

በአጋዴንም በምሥራቅና ምዕራብ ጋሻሞ፣ በካሉብና ጎዴ የነዳጅና ጋዝ ፍለጋና ቁፋሮ ሥራዎች፤ በባሕልና በትምህርት መስክ በተደረጉ ስምምነቶች ብዙ ኢትዮጵያዊያኖች ወደ ሩሲያ ተልከው ተምረው መመለሳቸው ለጤናማ ግንኙነታቸው ተጨማሪ ማሳያ ናቸው። እነዚህ በሩሲያ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ከሀገራቸው ባለፈ ለዓለምም የተረፉበት ሁኔታም ተፈጥሯል፡፡

ይህ በተለያዩ መንግሥታት የዘለቀው የሀገራቱ ግንኙነት በመርህ ላይ የተመሠረተ ለመሆኑ እምብዛም ማስረጃ የሚጠይቅ አይደለም፡፡በታላቅ ሀገርና በትንሽ ሀገር፣ በሀብታምና በድሃ መካከል የሚታይ ሳይሆን ሀገራት በዓለም አቀፍ መድረክ በእኩልነትና በፍትህ አደባባይ በእኩልነት ይታያሉ የሚለውን መርህ በተጨባጭ ተግባራዊ ያደረገ ነው፡፡

ዛሬ ስለ ዓድዋና ሊዎንቴቭን ስናስታውስ፤ ጠላት የፈለገውን ያህል መሣሪያ ታጥቆና ተደራጅቶ ቢመጣም ለነጻነት ካለን ቀናኢነት እና ለሀገር ካለን ፍቅር እንደማይበልጥ ነው። ለዚህ ደግሞ የዓድዋ ድል ሕያው ምስክራችን ነው።

# የኢትዮጵያን መጻዒ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ጃፋር በድሩ እንደሚሉት፤ ልብስን ለመስፋት መርፌው ቀድሞ መንገድ ሲመራ ክሩ ደግሞ እየተከተለ እንደሚያጸና ሁሉ የቀደመውን ትውልድ ህልሞች፣ ምኞቶች ፍላጎቶችና ጥያቄዎች መመለስ ይገባል። የተጀመሩ ውጥኖች መጻዒ እድሎችና ፈተናዎችን ለመሻገር ፋና ወጊ የሆነውን መስመር መከተልም ይገባል። ይህም የሚገለጸው በዓባይ ወንዝና በቀይ ባህር ላይ ያለው አቋም ነው።

በአሁኑ ወቅት ከመቼውም ጊዜ በላይ ውሃ በተለያዩ መስኮች አስፈላጊ የትኩረት አጀንዳ እየሆነ መጥቷል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በተለይም ለኢትዮጵያ የውሃ ሀብትን በስፋት መጠቀም ወሳኝ ጉዳይ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በውሃ ሀብት የታደለች ብትሆንም፤ ሀብቶቿን ተጠቅማ ብልጽግናዋን ከማስጠበቅ አንጻር ብዙ ሥራ ይጠበቅባታል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ሁለቱ የውሃ አካላት ላይ የሚንጸባረቁ ስትራቴጂዎች ሲኖሩ ኢትዮጵያ ችግሮቿን በሚገባ እየፈታችና ስብራቶቿን እየጠገነች እንደምትሄድም ያመላክታሉ።

ዳይሬክተሩ እንደሚያብራሩት፤ የዓባይን ወንዝ ተፋሰስ ተከትለው በምዕራብ አቅጣጫ የሚፈሱ ወንዞችና በምሥራቅ አቅጣጫ የሚገኘው የቀይ ባህር ክልል የኢትዮጵያን ዕድገትና ጥንካሬ፤ ውድቀትና ድክመት የሚተነብዩ ናቸው።

"ወደ ቀይ ባህር እየቀረብን ስንሄድ ታላቅነት፤ ከባህሩ እየራቅን ስንሄድ ደግሞ መዳከም እንደሚከሰት የታሪክ ዑደቶች በአንክሮ ያመላክታሉ" ሲሉ ዳይሬክተሩ ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ ነባራዊ ፍላጎቶቿን በሳይንሳዊ መንገድ ለማጥናት ከሚደጋገሙ ታሪኮቿ የዓባይና የቀይ ባህር ጉዳይ አንዱ መሆኑን በማንሳት፤ ስትራቴጂካዊ እይታዎችንና ትልሞችን በማፍለቅ መጻዒ በጎ ዕድሏን ማረጋገጥ እንደሚቻል ይጠቅሳሉ። ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ በዓባይና በቀይ ባህር ላይ ያላትን አቋም የሚያንጸባርቀውና "የሁለት ውሃዎች ዐቢይ ስትራቴጂ" የተሰኘው ታሪካዊ መጽሐፍ ሁነኛ ማሳያ እንደሆነም ይናገራሉ።

የስትራቴጂ መጽሐፉ ፋይዳው የጎላ መሆኑን የሚገልጹት ዳይሬክተሩ፤ በታሪክ ሂደት ችግር ሆነው ለዘለቁ ጉዳዮች መፍትሔ የሚሰጥ ከመሆኑ ባሻገር፤ የዓባይ ተፋሰስንና የቀይ ባህር ጉዳይን አንድ ላይ በማምጣት ልዩ ትኩረት መስጠቱን ያነሳሉ። ለሀገሪቷ መሪ ስትራቴጂና የትኩረት ማዕከል መሆኑን ይጠቅሳሉ።

የዓባይ ወንዝና ቀይ ባህር የኢትዮጵያ መጻዒ ተስፋ ናቸው የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ በተለይም የዓባይ ተፋሰሶችን በስፋት በመጠቀም የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባለፈ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ላላቸው ዘርፎች መጠቀም እንደሚገባ ይመክራሉ።

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ በዓለማችን በጣት ከሚቆጠሩ ወሳኝ ስትራቴጂካዊና ቁልፍ ስፍራዎች አንዱ ቀይ ባህር ነው። በዓመት ቢያንስ አንድ ትሪሊዮን ዶላር የሚጠጋ የባህር ላይ ንግድ መተላለፊያ መስመር ነው።

የቀይ ባህር ቀጣና የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና ሲጫወት የቆየ የውሃ አካል መሆኑን ጠቅሰዋል። ኢትዮጵያ ለባህሩ ስትቀርብ ማደግን ስትርቅ መውደቅን የምታይበት ታሪካዊ ሀቅ ነው።

ሀገሪቷ ወደ ውሃው በመቅረብ የምታገኘው ጥቅም ሲሰላ በርካታ መሆኑን አንስተው፤ ወደ ውሃ አካሉ እንዳትጠጋ ታሪካዊና ወቅታዊ ጠላቶቿ የሚያደርጉትን ርብርብ መቀልበስ እንደሚገባም ነው የሚያስገነዝቡት። ኢትዮጵያ ወደ ብልጽግና ለምታደርገው ጉዞ እነዚህ የውሃ አካላት ትልቅ ሚና እንዳላቸው ዳይሬክተሩ አመላክተዋል።

"የዓባይ ተፋሰስና የቀይ ባህር ቀጣና ለኢትዮጵያ እንደ ዓይን ብሌን የሚታዩ የብሔራዊ ደኅንነት ጉዳዮች ናቸው በማለት፤ ወደ ቀይ ባህር ለመመለስና የባህር በር ባለቤትነትን ለማግኘት የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት ትብብርን በማሳደግ አብሮ መልማት በሚቻልባቸው መንገዶች ዙሪያ ወሳኝ ስትራቴጂዎች መሰነዳቸውን ጠቅሰዋል።

የዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ መሐመድ ሀሰን በበኩላቸው፤ ሁለቱ የውሃ አካላት የሚታወቅ የሚመስል ነገር ግን ዝርዝሩ ጥልቅ የሆነ ጉዳይ ነው ይላሉ።

"ሁለቱ የውሃ አካላት ለምን ለኢትዮጵያ አስፈለጉ የሚለውን ተንትኖ መገንዘብ ካልተቻለ ወደ ፊት መራመድ አይቻልም።" የሚሉት አቶ መሐመድ፤ በዓባይም ሆነ በቀይ ባህር በኩል እንደ ሀገር ትልቅ እርምጃ መራመድ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

ሁለቱ የውሃ አካላት የኢትዮጵያን መጻዒ ዕድል የሚወስኑ እንደመሆናቸው ስሜት መር የሆኑ ምኞቶችን በመሻገር አንገብጋቢ ጥያቄዎችን በአግባቡ ማኖር የዚህ ዘመን ትውልድ ግዴታ መሆኑን በአጽንኦት ይናገራሉ።

ዓባይና ቀይ ባህር የኢትዮጵያ ወሳኞቹ አጀንዳዎች መሆናቸውን አንስተው፤ ሆኖም ትልቅ ጥቅም ባለበት ሁሉ ከባድ ጫኸቶችም እንደማይጠፉ ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ በዓባይ ግድብ ግንባታ፣ በአረንጓዴ አሻራ፣ በሌማት ትሩፋት፣ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች መርሀ ግብር የገጠሟት ተቃውሞዎች ብዙ መሆናቸውን በመግለጽ፤ አሁን ላይ በዓለም መድረክ እውቅናን እንዳገኘችባቸው አንስተዋል።

አሁን በውሃ ላይ የተጀመረው እንቅስቃሴም በርካታ ጫኸቶች ሊስተናገዱበት የሚችል ቢሆንም፤ ሀገር የጀመረችውን እርምጃ ግን ሳታቆም እጣፈንታዋን ለመወሰን በቁርጠኝነት መገስገሷን ነው የተናገሩት።

የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ከዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬትና ከአብርሆት ቤተ መጻሕፍት ጋር በትብብር ያዘጋጀው "የሁለት ውሃዎች ዐቢይ ስትራቴጂ" የተሰኘው መጽሐፍ እንደሚያትተው፤ ዓባይና ቀይ ባህር የኢትዮጵያን ደህንነትና ህልውና ከማስቀጠል አንጻር ቁልፍ ሚና አላቸው።

ኢትዮጵያ አሁን ከደረሰችበት ዕድገት በላይ ወደፊት እንድትሄድ ካስፈለገና በታሪክ በቀጣናው ላይ የነበራትን የጎላ ሚና ተመልሶ እንዲመጣ እነዚህ የውሃ አካላት ሚናቸው የጎላ ነው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ የቀይ ባህር ተጋሪ ከመሆኗ ጋር የተያያዘ እንደነበር የሚያትተው መጽሐፉ፤ አሁንም ቢሆን ወደ ባህር ተጋሪነቱ መማተር እንደሚገባት ያስቀምጣል።

ወደ ቀይ ባህር መማተርና ወደ ዓባይ ተፋሰስ የሚቀላቀላት ውሃ በአግባቡ መጠቀም እንደሚያስፈልግ በሚገለጽበት ጊዜ የውሃ አካላትን ለመንካት ሲታሰብ ተጨማሪ ስጋት እንደሚኖር መጽሐፉ ያመላክታል።

ኢትዮጵያ ወደፊት ለምታደርገው ጉዞ ችግሮች ሊገጥሙ ይችላሉ በሚል ስጋት አርፎ መቀመጥ ሳይኖርባት ይልቁንም የትኛውንም ችግር እንደየባህሪው እየተጋፈጠች ጥቅሟን እያስከበረች መሄድ እንደሚገባት አመላክቷል።

# ኢትዮጵያና ኬንያ በቀጣናው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የትብብር፣ የአጋርነት እና የወንድማማችነት ጎብረት አላቸው፡፡

ቀደምት መሪዎች በሠሩት ሥራ በሀገራቱ መካከል ግጭቶች እንደሌሉ በመግለጽ፤ የሁለቱ ሀገራት መሪዎች በሁለትዮሽ ትብብር ላይ ሰፊ ውይይት ማካሄዳቸውን ጠቁመዋል፡፡

በውይይታቸው በተለይም ቀደም ሲል በአዲስ አበባ የኢትዮ-ኬንያ የሚኒስትሮች ጥምር ምክር ቤት በደረሰው ስምምነት ሀገራቱ ሰባት ስምምነቶችን እንደተፈራረሙ አንስተዋል፡፡

ስምምነቱ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በደህንነት ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ጠቅሰው፤ ቀደም ባሉት ጊዜያትም የተፈረሙ ስምምነቶች የሚጠናከሩበት እና የሚሰፉበት ጉዳይ ላይ እንደመከሩ ገልጸዋል፡፡

ሀገራቱ በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ በመሆናቸው ከተለዋዋጩ እና ከአዳጊው የዓለም ሁኔታ ጋር በሚሄድ መልኩ የሁለቱ ሀገራት የደህንነት ሁኔታ መጠናከር በሚችልበት ላይም መምከራቸውን ጠቁመዋል፡፡

በተለይም በቀጣናው እንደ ስጋት የሚታየው አልሸባብ በሁለቱም ሀገሮች ላይ ጥቃት የሚፈጽም በመሆኑ ይሄንን በጋራ በሚመክቱበት እንዲሁም ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ተወያይተዋል ነው ያሉት፡፡

በተጨማሪም የኢኮኖሚ ትብብር ግንኙነቱ የሚጠበቀውን ያህል አለመሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ በዘርፉ ላይ ያለው ግንኙነት በሚጠናከርበት ሁኔታ ላይ ምክክር ተደርጓል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለኬንያ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማቅረብ ኬንያም ከኢትዮጵያ ገዝታ ለመጠቀም ከስምምነት ላይ ተደርሶ የኤሌክትሪክ ማሰራጫ መስመሮችም ተዘርግተዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ የወደብ አማራጮቿን እያሰፋች ነው ያሉት ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር)፤ የሁለቱ ሀገራት መሪዎች በመንገድ አቅርቦት እንዲሁም በዲጂታል ኢኮኖሚና ደህንነት ላይ በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን ውይይት አካሂደዋል ብለዋል፡፡

ድህነትን ለማስወገድ የሀገራቱን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ማጠናከር፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማጎልበት እንዲሁም የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ውይይት መካሄዱንም ተናግረዋል፡፡

በኬንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ባጫ ደበሌ በበኩላቸው፤ በመንግሥት በኩል ኢትዮጵያና ኬንያ የነበራቸውን የቀደመ ግንኙነት የሚያጠናክር ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ሀገራቱ ረጅም ዕድሜ ያለው ልዩ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዳላቸው ገልጸው፤ ግንኙነቱ እስከ ወታደራዊ ውል ድረስ የዘለቀ እንደነበር አንስተዋል፡፡

ወታደራዊ ውሉ ኢትዮጵያ ችግር ሲገጥማት የኬንያ ወታደር ለኢትዮጵያ እስከ መዋጋት እንዲሁም ኬንያ ችግር ሲገጥማት የኢትዮጵያ ወታደር ለኬንያ እስከ መዋጋት የሚደርስ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩልም ኢትዮጵያ ከኬንያ ጋር ሰፊ ድንበር የምትጋራ መሆኗን ጠቅሰው፤ በድንበር አካባቢ ምንም ዓይነት የሰላም እጦት ሀገራቱ ገጥሟቸው እንደማያውቅ አመልክተዋል።

ይህንንም ጠብቆ ለማስቀጠል የሚኒስትሮች ጥምር ምክር ቤት እንዳላቸው አውስተዋል፡፡

ይሁንና ይህ ትልቅ ፋይዳ ያለው ጥምር ምክር ቤት ላለፉት ሰባት ዓመታት ተቋርጦ እንደነበር ገልጸው፤ ጥምር ምክር ቤቱ በዚህ ወር የጋራ ስብሰባውን በማድረግ የተለያዩ የጋራ መግባቢያ ስምምነቶችን እንደተፈራረመ ተናግረዋል፡፡

በዚህም በፀጥታ፣ በቱሪዝም፣ በግብርና እና ኤሌክትሪክ ኃይልን ጨምሮ ሀገራቱ በሰባት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የመግባቢያ ስምምነት መፈራረማቸውን አብራርተዋል፡፡

የመግባቢያ ስምምነቱን ተከትሎም የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ የፀጥታ ጉዳይን በተመለከተ ከኬንያ አቻቸው ጋር እንደሚመክሩ ጠቁመዋል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኬንያ ጉብኝት የሁለቱን ሀገራት የቆየ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሻግርና ወደ ፊት ለመሥራት የታሰቡትን ሥራዎች በጥሩ ሁኔታ ለመሥራት አጋዥ ይሆናል ብለዋል አምባሳደር ባጫ፡፡

# በኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የዲፕሎማሲ ሳምንት መጠናቀቅን አስመልክቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትናንት መግለጫ ሰጥቷል።

መግለጫውን የሰጡት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ በርካታ ዘመናትን ያስቆጠረ ነው። ይህን መነሻ በማድረግ ‹‹የዲፕሎማሲ ሳምንት›› በሚል ርዕስና "ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን" በሚል መሪ ቃል ከጥር ሁለት ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ የነበረው ኤግዚቢሽን ለተከታታይ 48 ቀናት ለጎብኚዎች ክፍት ሆኖ ቆይቷል። በውጤት ተጠናቅቋል ብለዋል።

እንደ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ ገለጻ፤ ከዲፕሎማሲ ሳምንቱ ኤግዚቢሽን በርካታ ውጤት ተገኝቷል። በኤግዚቢሽኑም ሀገሪቷ ከበርካታ ሀገራት ጋር የመሰረተቻቸው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ተዳስሰዋል።

ግንኙነቶችን በማስፋፋት ብሔራዊ ጥቅሟን አስከብራ ለመዝለቅ ያደረገችውን ረጅም የዲፕሎማሲ ጉዞ በዲፕሎማሲ ሳምንት በኤግዚቢሽን ቀርቧል ብለዋል።

የሀገራችን ብሔራዊ ጥቅም በማስጠበቅ የመጪውን ዲፕሎማሲ በአዲስ አስተሳሰብ የተቃኘበት ነው ያሉት አምባሳደሯ፤ ኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን አስጠብቃ ለመሄድ የሚያስችላትን የዲፕሎማሲ ፍኖተ ካርታ በማመላከት ንቅናቄ የሚያስፈልግ መሆኑን ማሳየት የሚል ዓላማ እንደነበረው አምባሳደሯ ገልጸዋል።

ኤግዚቢሽኑ ከተጀመረ ጀምሮ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኚዎች መጎብኘታቸውን የገለጹት አምባሳደር ብርቱካን፤ ከጥር 2 ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 48 ቀናት ውስጥ ስድስት መቶ 39 ተቋማትና ከ250 ሺህ በላይ ዜጎች መጎብኘታቸውን ጠቅሰዋል። ይህም ኤግዚቢሽኑ በውጤት መጠናቀቁን ያመላክታል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በጥንትና በመካከለኛ ዘመን የነበራትን ዲፕማሲያዊ ግንኙነት ማስገንዘብ ተችሏል ያሉት አምባሳደሯ፤ ከ116 ዓመታት ጀምሮ ዘመናዊ የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ተዳሰዋል። ኢትዮጵያ የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ በዓለም አቀፍ ተቋማት መስራች በመሆን ለጥቁር ሕዝቦች ፍትህና እኩልነት እንዲመጣ የነበራትን ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶችና ያሳረፈቻቸው አሻራዎች ተሰንደው ተዘክረዋል ነው ያሉት።

በለውጥ ማግስት በውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን ላይ ለውጦች ተደርገዋል ያሉት አምባሳደሯ፤ ዲፕሎማሲያችን መሰረት ያደረገው የዜጎች ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣ ለጎረቤት ሀገራት ቅድሚያ መስጠትን፣ ቀጣናዊ ትስስርን ማጠናከርና ለአፍሪካዊ ተግዳሮት አፍሪካዊ መፍትሔ ተግባራዊ ማድረግን መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን ከሁሉም ሀገራት ጋር የባለብዙ ወገን የዲፕሎማሲ መድረኮች ትብብር ማጠናከር እንደሚያስፈልግ በማመን ሠርታለች። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የጸጥታው ምክር ቤት አሠራርና አደረጃጀት እንዲሻሻል አስተዋጽኦ አድርጋለች ብለዋል።

እንደ አምባሳደሯ ማብራሪያ፤ የዲፕሎማሲ ሳምንት ኤግዚቢሽኑን እንዲሳካ በርካታ ተቋማትና ግለሰቦች ከፍተኛ አበርክቶ ነበራቸው። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አመራሮችና ባለሙያዎች ኤግዚቢሽኑ ተጀምሮ ለዕይታ ክፍት እንዲሆን ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ኤግዚቢሽኑ በተለያዩ ዲዛይኖች ሳቢና ውብ በሆነ መልኩ ለጎብኚዎች እንዲደርስ ቀን ከሌት የሠሩ መሆናቸውን በመግለጽ ምስጋና አቅርበዋል።

# "በውይይት፣ በንግግርና በምርጫ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በውይይታቸው ወቅት እንደገለጹት፤ በወይይት፣ በንግግርና በምርጫ እያመንን ብንሄድ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም ብቻ ሳይሆን ፈጣን ልማት ይመጣል፡፡

ዶክተር ዐቢይ አክለውም ችግሮች አሉ ለመቅረፍ እየተሠራ ነው፤ ነገር ግን ችግርን ብቻ በማየት ልማት ማምጣት አይቻልም ብለዋል፡፡

በተደረጉ ሕዝባዊ ወይይቶች ጠቃሚ የሆኑ ግብዓቶች መገኘታቸውን ዶክተር ዐቢይ ተናግረዋል፡፡

ልማት በተሟላ ሁኔታ ምላሽ የሚያገኘው በትውልድ ቅብብሎሽ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በአንድ ትውልድ ተጀምሮ የሚያልቅ እንዳልሆነ ተናግረዋል፡፡

እንደ ዶክተር ዐቢይ ገለጻ፤ መንግሥትም ወደ ሕዝብ ቀረብ ብሎ ማድመጥ ሕዝብም ሀገር ያለችበት ሁኔታ መገንዘብ ይኖርበታል፡፡ ይህን እውን ማድረግ ሲቻል ልማት ማምጣት አያዳግትም፡፡

መሠረተ ልማት በሁሉም ክልሎች ጥያቄ በሆነበት ሀገር ከፍተኛ የሆነ ኢንቨስትመንት ስለሚፈልግ በሕዝብ የተነሱ ጥያቄዎች አቅም በፈቀደ መልኩ ደረጃ በደረጃ የሚመለስ መሆኑንም ነው ዶክተር ዐቢይ ያመላከቱት፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም፤ ከዚህ በፊት የተለያዩ ተስፋ የተጣለባቸው መሠረተ ልማቶች በጅምር የቀሩበት ሁኔታ ነበር፡፡ አሁን ላይ ከመሠረተ ልማትና እድገት አኳያ በሁሉ ዘርፍ ተስፋ ሰጪ በመሆኑ ይህንን መገንዘብ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በመሠረተ ልማት ዘርፍ ከፍተኛ ዕድገት ቢኖርም ተጨማሪ ሥራዎች መሥራት እንዳለባቸው ያመላክታል ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ ከግማሽ ትሪሊዮን በላይ ብር እየወጣ ያለው ከባለፉት ከተጀመሩትና በአዲስ የተጀመሩ የመንገድ መሠረተ ልማት ሥራ ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ሁለቱን ትላልቅ ግድቦችና ሌሎች የኃይል ፕሮጀክቶችን ጨምሮ የኢትዮጵያ መብራት ኃይል 350 ቢሊዮን ብር ፕሮጀክት ይዞ እየሠራ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ከወሰን ጋር ተያይዞ በሰጡት ምላሽ፤ በክልሎቹ መካከል ወይይት መደረግ አለበት ብለዋል፡፡ የፌዴራል መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የተያዙ የመንገድ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ያለመፋጠን፣ የተለያዩ መሠረተ ልማት ችግር፣ የሰላምና የሕግ የበላይነት አለመከበር እና የወሰን ግጭቶች መፍትሔ ያለማግኘት በተወያዮች የተነሱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ተወያዮቹ ግብርናውን ያለማዘመን፣ ትክክለኛ የንግድ ሥርዓትና የገበያ ትስስር አለመኖር እና ጦርነት በነበሩባቸው አካባቢዎች መልሶ ማቋቋም አለመቻል እንዲሁም የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎችን በቂ ትኩረት አለማግኘት የሚሉትን ጥያቄዎችም በተመሳሳይ አንስተዋል፡፡

ተሳታፊዎቹ የዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየምና ሌሎች ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች ማየታቸው እንዳስደሰታቸው ገልጸው፤ እንደዚህ ዓይነት የልማት ሥራዎች ወደ ክልል እንዲወርዱ ጠይቀዋል፡፡

# ሕክምና ከመስጠት ባሻገር ሰብዓዊነት የጎላበት የባለሙያዎች ስብስብ

ሰሚራ በርሀ




ለአንድ ተቋም መመስረት የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ምክንያቶች የአንድን ሰው ሀሳብ እና ጊዜ ከመውሰድ፣ ለብቻ ከመብሰልሰል አልፎ ምናልባትም በሌሎች ልብ ውስጥ ጭምር ያሉ ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይሁንና ሀሳቡን አንድ ሰው ደፍሮ ወደፊት ያምጣው እንጂ ብዙዎች ይጋሩታል። ብዙ ወደፊት የመጡ ሀሳቦችም ደግሞ ብዙዎች ተጋርተውት መፍትሄ ሲሆን መመልከት የተለመደ ነው፡፡

የዛሬው የ‹‹ሀገርኛ›› አምዳችንም ትኩረቱን በዚሁ ሀሳብ ላይ አድርጓል፡፡ ሃሳቡ በተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ ላይ በተሰማሩ ባለሙያዎች ልብ ተጠንስሶ በርካታ ቁጥር ላላቸው ሴቶች መፍትሔ መሆን ችሏል። በጤናው ዘርፍ የራሱን ድርሻ በመወጣት ሴቶችን እያገዘ ያለው ‹‹የሴቶች ጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅት›› ነው፡፡

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ውስጥ የሕጻናት ሕክምና፣ የአዋቂዎች ሕክምና፣ የውስጥ ደዌ፣ የካንሰር ሕክምናዎች ይሰጣሉ፡፡ የማህጸን እና ጽንስ ሕክምና ክፍል ከሆስፒታሉ የሕክምና ዘርፎች መካከል አንዱ ነው፡፡ በሆስፒታሉ የተቋቋመው ‹‹የሴቶች ጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅት›› በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ውስጥ ባሉ የማህጸን እና ጽንስ የሕክምና ክፍል ዶክተሮች፣ ስፔሻሊስቶች፣ የስፔሻላይዝድ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች በሕብረት የተቋቋመ ሲሆን፤ ትኩረቱን የካንሰር ታማሚዎችን ለማገዝ የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡

ዶክተር ወንድሙ ጉዱ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የማህጸን እና ጽንስ ሀኪም እና የማህጸን እና ጽንስ ሕክምና ክፍል ኃላፊ እንዲሁም ‹‹የሴቶች ጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅት›› ዋና ስራ አስኪያጅ ናቸው፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ ይህንን በሴቶች ጤና ላይ ያተኮረ የበጎ አድራጎት ድርጅት ለማቋቋም ምክንያት የሆናቸው በየዕለቱ በሆስፒታሉ ውስጥ የሚያስተናግዷቸው ታካሚዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ታካሚዎች በጽኑ ሕሙማን ክፍል የሚገኙ የካንሰር ሕክምና ላይ ያሉ ሲሆኑ ለሕክምና በሚመጡበት ወቅት ያልታሰበ የሕክምና ወጪ ይገጥማቸውና የሕክምና ወጪያቸውን ለመሸፈን ይቸገራሉ፡፡ የስነተዋልዶ ጤና ቅድመ ምርመራ ለማድረግ ግንዛቤ እና ወጪ የመሸፈን አቅም የሌላቸው ሴቶች እና ልጃገረዶች መኖራቸው እንዲሁም ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ የስነ ተዋልዶ ጤና ምርመራ ማድረግ የማይችሉ በርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎች መኖራቸው ይህንን ተቋም ለመመስረት እንደምክንያትነት ተቀምጧል፡፡

ወደ ሆስፒታሉ ይዘውት የመጡትን ታካሚ ለማስታመም እና ወደሚያስፈልገው የምርመራ ክፍል ለመውሰድ የታዘዘለትን መድሀኒት ለማምጣት የሚሯሯጡ አስታማሚዎች፣ በየሕክምና ክፍሉ ኮሪደር ላይ በደከመ መንፈስ ቆመው ተራቸውን የሚጠብቁ ታካሚዎች፣ በሁሉም የአገልግሎት መስኮች ላይ ትንሽ የማይባሉ ሰልፎች በሆስፒታሉ ውስጥ የተለመዱ ናቸው።

ታዲያ በዚህ ልባቸው የተጨነቁ እና እርዳታ የሚፈልጉ ታካሚዎችና የታካሚው ቤተሰቦች መሀል በትልቅ አክብሮት የሚታዩ የችግሩ መፍትሄ ሰጪ ተደርገው የሚወሰዱት የጤና ባለሙያዎች ይገኛሉ። ዶክተሮችም ቢሆኑ ስራቸው ሰውን ማከም ነውና የተቻላቸውን ሁሉ በማድረግ ታካሚዎቻቸውን ያስተናግዳሉ፡፡ አንድ ሀኪም እና ታካሚ ያላቸው ግንኙነት በአንድ ሆስፒታል ውስጥ አልያም በአንድ ጠባብ ቢሮ ውስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ በተለይም ደግሞ ተከታታይ የሆነ የሕክም ክትትል የሚያደርጉ ታካሚዎች ከሐኪሞቻቸው ጋር የቤተሰብ ያክል ቅርርብ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የአንድ ሐኪም እፎይታ በየዕለቱ ታካሚዎቹ ላይ በሚያየው ፈገግታ ይወሰናል፡፡

ሆስፒታሎች የሰው ልጅ ወደ ምድር የሚመጣበትንና የምድር ቆይታ ማብቂያንም የሚያስተናግዱ ሲሆን አንዳንዶች በሆስፒታል ውስጥ የሚከሰት ሞት ለጤና ባለሙያዎች የተለመደ ስሜት አድርገው ይወስዱታል። ነገር ግን የጤና ባለሙያዎቹ እንደሚናገሩት፣ አንድን ታካሚ ማዳን ሳይቻል ቀርቶ ሕይወቱ ሲያልፍ እንደማየት ልብ የሚሰብር ነገር ለጤና ባለሙያ የለም፡፡ አንድ ታካሚ በሆስፒታሉ ውስጥ በሚያደርገው ሕክምና የሚጠየቀውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል ሳይችል ሲቀር፣ የታዘዘለትን መድሀኒት ለመግዛት እጅ ሲያጥረው፣ ከፋ ሲል ደግሞ ያላሰበው የበሽታ አይነት ተነግሮት ከፍተኛ ገንዘብ ሲጠየቁ አስታማሚዎች ብቻ ሳይሆኑ የጤና ባለሙያዎችም እኩል ያዝናሉ፡፡ ባለሙያዎቹ ታዲያ አዝነው ብቻ አይቀሩም ኪሳቸውን ፈተሽ ፈተሽ አድርገው የስራ ባልደረባቸውን አስተባብረው የታካሚዎችን ችግር መጋራት የሁሉም የጤና ባለሙያዎች የሚጋሩት የእለት ተዕለት ክስተት ነው፡፡

በሆስፒታል ውስጥ አንድ አስታማሚ የታካሚውን ሕክምና ለማድረግ የሚጠየቁ እቃዎችን መድሀኒቶችን እየገዛ ባለበት ወቅት በእጁ ያለ ገንዘብ ሊያልቅበት ይችላል፡፡ አልያም ደግሞ ከተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚመጡ ታካሚዎች በቂ ገንዘብ ሳይኖራቸው ነገር ግን ሕይወታቸው ይቀጥል ዘንድ መታከማቸው የግድ ሆኖ ባዶ እጃቸውን በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ታዲያ ለእነዚህ የተጨነቁ ሰዎች በቅድሚያ የሚደርሱላቸው የሕክምና አገልግሎት የሚሰጧቸው የጤና ባለሙያዎች ናቸው።

ከሙያቸው ባሻገር ከኪሳቸው አውጥተው ይህንን ታካሚ በቻሉት መጠን ያግዙታል፡፡ በዙሪያቸው ያሉ የሙያ አጋሮቻቸውን እንዲሁ አስተባብረው ገንዘብ በማሰባሰብ የቻሉትን ያደርጋሉ፡፡ ይህ በአንድ ሆስፒታል ውስጥ የተለመደ ተግባር እንደሆነ የጤና ባሙያዎቹ ያነሳሉ፡፡ እነዚህ የጤና ባለመያዎች ታዲያ ከኪሳቸው አውጥተው የሚሰጡት ገንዘብም ሆነ በሰዓቱ የሚያደርጉት ድጋፍ በዘላቂነት ችግሩን የማይፈታው በመሆኑ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ በልባቸው ሲያብሰለስሉት ቆይተዋል፡፡ ሀሳቡ በሁሉም ልብ ውስጥ የነበረ ነውና በየግላቸው የሚያደርጉትን ድጋፍ ወደ አንድ የተሻለ ተቋማዊ መልክ መስጠት የሚለውን ሀሳብ በቀላሉ ሊያግባባቸው ችሏል፡፡

በመሆኑም የጤና ባለሙያዎቹ ድጋፋቸውን በዘላቂነት ለማስቀጠል አስቀድመው እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ታካሚዎች ተደራሽ የሚሆን ቋሚ የሆነ የመዋጮ ስርዓት (Patient Fund Committee) በመዘርጋት ከወር ደሞዛቸው ላይ ተቆራጭ የሚያደርጉበትን መንገድ ጀምረዋል፡፡ ነገር ግን በዚህ ብቻም ሳያበቃ ከወርሀዊ መዋጮው ባሻገር ተጨማሪ ገንዘብ ከኪሳቸው የሚያወጡ ባለሙያዎች ነበሩ፡፡

በሆስፒታሉ ውስጥ የማህጸን እና ጽንስ ሕክምና ክፍል ውስጥ ያሉ ዶክተሮች ይህንን ሀሳብ ሲያመጡ ስፔሻላይዜሽን ትምህርት የሚማሩ የጤና ባለሙያዎች እንዲሁ በየግላቸው የሚያደርጉት ድጋፍ አቅም ኖሮት ተቋማዊ ስርዓት እንዲኖረው ሀሳባቸው ይዘው ወደ ባልደረቦቻቸው መጡ፡፡ ይህ ሀሳብም በሁሉም ዘንድ ስምምነት ላይ ደርሶ ማኅበር ለማቋቋም የመጀመሪያ ስብሰባቸውን አድርገዋል፡፡ የማህጸን እና ጽንስ ሀኪም ክፍል ሐኪሞች እንደመሆናቸውም በየእለቱ በሕክምና ክፍል ውስጥ የሚያስተናግዷቸው ሴት ታካሚዎች ጤና በእጅጉ አሳስቧቸው ነበርና ‹‹የሴቶች ጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅት›› የሚል ስያሜ ሰጡት፡፡ አስፈላጊ ሰነዶችን በማዘጋጀት ሕጋዊ እውቅና እንዲሰጣቸው ለኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ጥያቄያቸውን አቀረቡ፡፡

እንደ ዶክተር ወንድሙ ገለጻ፣ ድርጅቱ ከመቋቋሙ በፊት ከወር ደመወዝ ተቆራጭ ከሚደረግ እገዛ ውጪ በአቅራቢያቸው ካሉ ፈቃደኛ ሰዎች በሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ 70 ለሚደርሱ ታካሚዎች የሕክምና አገልግሎት መስጠት የቻሉ ሲሆን፤ ይህም በገንዘብ ሲተመን 150 ሺህ ብር የሚደርስ እርዳታ ማድረግ መቻሉን ነው ያስረዱት፡፡

ምንም እንኳን መነሻው ሕክምናቸውን እየተከታተሉ የገንዘብ እጥረት የገጠማቸው ሰዎችን በመርዳት ተጀመረ እንጂ ከሆስፒታሉ ውጪ የሚገኙ ሴቶችን ተደራሽ ለማድረግ፣ አስቀድሞ የመከላከል ስራንም ያካተተ እንደሚሆን በምርቃት ቀኑ ላይ ተጠቅሷል፡፡ የቅድመ ካንሰር ምርመራ እድሎችን ማመቻቸት፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋጀት፣ ወደ ሆስፒታሉ መጥተው መታከም ላልቻሉ ሴቶች ያሉበት ድረስ በመሄድ የቅድመ ካንሰር ምርመራዎችን በማድረግ የአገልግሎት አድማሱን በማስፋት ከጤና ተቋማት ውጪ ከቀያቸው ተፈናቅለው በማቆያ ቦታዎች፣ በጎዳና ላይ ያሉ ሴቶችን ተደራሽ በማድረግ የሴቶችን ጤና ለመጠበቅ እና ግንዛቤያቸውን ከፍ ለማድረግ ይሰራል፡፡

ይህ በአንድ ክፍል ውስጥ የተጀመረ ሀሳብ አድጎ ራሱን የቻለ ተቋም ለመሆን ሲታሰብ በቅድሚያ የኮሌጁ አስተዳደር አካላት ተቋማዊ አሰራር እንዲኖረው ከሀሳብ ጀምሮ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ የድርጅቱ ዓላማም በሕክምና ላይ የሚገኙ የገንዘብ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ታካሚዎች እገዛ ማድረግ፣ ወደ ማኅበረሰቡ በመዝለቅ ካንሰር ከመከሰቱ በፊት ለመከላከል የሚያስችሉ የቅድመ ካንሰር ምርመራዎችን ማመቻቸት እና በተለያዩ ተቋማት በመገኘት የሴቶች ጤናን የተመለከቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ሴቶች ግንዛቤው እንዲኖራቸው በማድረግ የበሽታ ስርጭቱን መግታት ይቻል ዘንድ ይሰራል። ከዚህም ባሻገር በሀገር ደረጃ የሚወጡ ጤና ተኮር ፖሊሲዎች ሴቶችን ያማከሉ ይሆን ዘንድ ተጽዕኖ መፍጠር የሚያስችሉ ስራዎችን መስራት በእቅዱ ውስጥ የተካተቱ ናቸው፡፡

እነዚህን ዓላማዎች የያዘው ‹‹የሴቶች ጤና ድጋፍ የበጎ አድራገጎት ድርጅት›› በ10 መስራች አባላት እና በስምንት የቦርድ አባላት በታህሳስ ወር 2016 ዓ.ም ህጋዊ ፍቃድ አግኝቶ ተመስርቷል፡፡ በምርቃት ስነ-ስርዓቱ ላይም በሆስፒታሉ ውስጥ የሚገኙ የሌላ የሕክምና ክፍል ባለሙዎች እና የአስተዳደር ኃላፊዎች የኮሌጅ ዲኖች የተገኙ ሲሆን ሀሳቡ ብዙዎች የሚጋሩት እና መልካም ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ ተገልጿል፡፡ በሆስፒታሉ ከሚገኘ ማኅበረሰብ ውስጥም ድርጅቱ ከአንድ ሺህ እስከ አንድ ሺህ 500 አባላት ይኖሩታል ተብሎ እንደሚጠበቅም ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል። ማኅበሩ እውቅና የተሰጠው ተቋም በመሆኑ ዓላማውም በአንድ የሕክምና ተቋም ውስጥ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም እና በጎ ሀሳቡን ለሚደግፉ ሁሉ ክፍት ሆኗል።

ድርጅቱ ለታካሚዎች እገዛ ከማድረግም ባሻገር በሆስፒታሉ ውስጥ ሊገኙ የማይችሉ መመርመሪያ መሳሪያዎችን ከሌሎች ተቋማት ጋር በመነጋገር እና ግንኙነት በመፍጠር እንዲኖሩ የማስቻል እቅድም አለው፡፡ ሴቶች ሕይወትን የሚሰጡ ናቸውና የሴቶች ጤና ማለት የአንድ ሰው ጤና፤ የአንድ ቤተሰብ ጤና ሳይሆን የኅብረተሰብ ጤና አለፍ ሲል ደግሞ የሀገር ጤናም ጭምር ነው፡፡ ‹‹ሴት ጤና ስትሆን ሀገር ጤና ትሆናለች›› በሚል ሀሳብ ተቋቁሟል፡፡

ማኅበሩ ለሚያደርገው የገንዘብ ድጋፍ የተለያዩ አባላትን ባለሀብቶችን በመደገፍ እና የገቢ ማሰባበሲያ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ይሰራል፡፡ የድርጅቱን መመስረት በማብሰሪያው እለትም የደም ልገሳ ፕሮግራም የተካሄደ ሲሆን ይህ መልካም ሀሳብ በሌሎች የሕክምናና የትምህርት ክፍሎችም መልካም ተሞክሮ መሆኑ ተነስቷል፡፡ በሀገራችን ብሂል ‹‹ችግር በቅቤ ያስበላል›› እንደሚባለው ባለሙያዎች የተመለከቱት ችግር ከሆስፒታሉ ማኅበረሰብ አልፎ ለሌሎች መድረስ የሚችልበት መንገድ መፈጠሩም እንደ መልካም የሚጠቀስ ነው፡፡

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## የዓድዋን ድል መሠረት አድርጎ ነገ የራስን ታሪክ ለመስራት

እፀገነት አክሊሉ

የዓድዋ ድል ሁሉም ኢትዮጵያዊ ደምና አጥንቱን የገበረበት ነው። የዓድዋ ድል ለአሁኑ ትውልድ አብሮነትን፣ ሕብረትን፣ መደማመጥንና በጋራ መቆምን ያስተምራል። ኢትዮጵያውያን በብሔር፣ በሃይማኖት፣ በባህልና በቋንቋ ወዘተ ሊለያዩ ይችላሉ፤ ነገር ግን የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ዘመናት የተሻገረና ሌላው ዓለም ትምህርት የወሰደበት የአብሮነት እሴት አላቸው። ይህንን መልካም እሴት ሊንከባከቡትና ጠብቀው ሊያቆዩት ይገባል።

ሀገራችን አሁን ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ ስንመለከት በአንድ በኩል በውስጥና በውጭ ኃይሎች ሴራ አገርን የማተራመስ በሌላ በኩል ደግሞ የማፍረስ ጥረት ከመቼውም ጊዜ በላይ የታየበት፤ ከድህነትና ኋላ ቀርነት ጋር ከፍተኛ ግብግብ ውስጥ የተገባበት ነው። በዚህ ወቅት አገርን መታደግ የሚቻለው በአንድነት በመቆም ብቻ ነው። ኢትዮጵያን ከወቅታዊ ፈተናዎች መታደግ፣ የበለጸገችና ለዜጎቿ ምቹ የሆነች አገር ለቀጣዩ ትውልድ ማስረከብ ከዓድዋ ድል የምንማረው ሌላኛው ገጽታ ነው።

አሁን የተጋረጡብንን ችግሮች ልንፈታ የምንችለው ስንደማመጥና አንድ ሆነን ስንቆም ብቻ ነው። አለበለዚያ ግን የሚገጥሙን ማናቸውም ፈተናዎች የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ሊያንበረክኩን እንደሚችሉ ግልጽ ነው። “ካልተደራጀ ትልቅ ሀገር የተደራጀች ትንሽ መንደር ትልቅ ስራ ትሰራለች” እንደሚባለው ችግሮቻችንን ለመወጣት በአንድነት አብሮ መቆም ምን ያህል ትርጉም እንዳለው የዓድዋ ድል ህያው ማሳያ ነው።

ኢትዮጵያ ዜጎቿ በአንድነት የሰሯት፣ አንድነታቸውን ያስመሰከሩባት፣ በጥረታቸው ነፃነቷን ጠብቀው ለትውልዱ ያቆዩዋት አገር ነች። ዓድዋ የአባቶችን ታሪክ ተገንዝቦ፤ ያወረሱንን መልካም ገጸ በረከት ማስቀጠልና ለቀጣዩ ማስተላለፍ የሚችል ትውልድ መሆን እንደሚገባ ያስታውሰናል። የዓድዋ ድል ስኬታማ የሆነው በመላ ኢትዮጵያውያን የአንድነት መንፈስ በመሆኑ አሁንም ሆነ ወደፊት የአገራችንን እድገትና ብልጽግና የምናረጋግጠው አንድ ላይ በመቆም ብቻ ነው።


የአገር ጉዳይ ሲነሳ በየዘመናቱ እየመጣ የሚሄድ ትውልድ የራሱን ታሪክ ሠርቶ ያልፋል። የሚሠራው ታሪክም ዘመኑ በሚጠይቀው ዕውቀት፣ ዕሳቤ፣ የአገር ተጨባጭ ሁኔታና ዓለም አቀፋዊ ጫና ጭምር ነው። በዚያን ዘመን የነበሩ ሰዎች እንደተባለውም በተገለጸላቸው መጠን ታሪክ ሠርተው አልፈዋል። የአገርን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን ከወራሪዎችና ከተስፋፊዎች ጋር በመፋለም አስከብረው ነፃ አገር ለመጪው ትውልድ አስረክበዋል።

እንደሚታወቀው አውሮፓውያን በበርሊን ኮንፈረንስ በወሰኑት መሠረት አፍሪካን ዕጣ ተጣጥለው እንደ ቅርጫ ሲቃረጡ፣ ብቻዋን ቅኝ ገዥዎችን ተፋልማ ያልተደፈረች አገር ኢትዮጵያ ነበረች። ጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን ይህንን በመሰለ የጀግንነት ተጋድሎ የሚያኮራ ታሪክ ሠርተው ሲያልፉ፣ ተከታዩ ትውልድ እንደተባለው በጎደለው እየሞላ የራሱን ታሪክ መሥራት ይገባው ነበር። የሚሠራው ታሪክ አኩሪ እንጂ አንገት የሚያስደፋ እንዳይሆንም መጠንቀቅ ነበረበት። ከዚያ ውጪ ትናንት የጎደለውን ወይም የተዛነፈውን ዛሬ እየሞሉና እያስተካከሉ በዕድገት መራመድ ሲገባ፣ የትናንቱ ትርክት ላይ ተቸንክሮ እግርን መጎተት ፋይዳ ቢስ ነው። ለዘመኑ የዕድገት ደረጃም አይመጥንም።


አሁን ላይ እዚህም እዚያም የፖለቲካ ስልጣንና የኢኮኖሚ የበላይነት ለመያዝ ፍላጎት ያላቸው ኃይሎች፣ ወጣቶችን ያልተገባ ሳጥን ውስጥ በመክተት የኢትዮጵያ ሰላም እንዲደፈርስ ጥረት ማድረጋቸው የቀደመውን አርበኞች ታሪክ መዘንጋት ይሆናል። አገሪቱ አሁን የገጠማት ፈተና በአድዋ ጦርነት ከገጠማት ችግር አይበልጥም ወጣቶች የታሪክ ባለእዳ መሆናቸውን ተገንዝበው ኃላፊነታቸውን ከተወጡም እዳው ገብስ ነው።

የዓድዋ ድል ትውፊት ከአገር አልፎ ዓለም አቀፋዊ ሲሆን፤ በጥንት አባቶችና እናቶች የደም ዋጋ የተገኘው የዓድዋ ድል የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ታሪክ መሆኑ ሁሉም ይህንን ታሪክ ሊዘክረው ይገባል።


የኢትዮጵያውያንን የጋራ የድል ታሪክ ወደ ጎን በመተው ዛሬ ላይ የጎጠኝነት ዝንባሌዎች እንዲፈጠሩና አንዱ ሌላውን በጥርጣሬ እንዲመለከተው ማድረግ ተገቢ ባለመሆኑም በተለይ ወጣቱ ለግል ጥቅማቸው ብለው




ወጣት ያሬድ ሳቀው



ወጣት እንዳልካቸው ተስፋዬ



ወጣት ረመዳን ኑር ጌታ

ትልቁን ታሪካዊና አገራዊ ስዕል እንዳያይ ከሚያደርጉት አካላት ፖለቲከኞች በሚቀዱለት ቦይ ውስጥ መፍሰስ የለበትም። በመሆኑም ጀግኖች አባቶችና እናቶች ለአገራቸው ሲሉ ከፈፀሙት አኩሪ ገድል ብዙ ልንማር ይገባል።

ኢትዮጵያ በየጊዜው የሚነሱባት ጠላቶቿን እንድትመክትና ሽንፈት እንዲቀዳጁ ምክንያት የሆነው፣ ሕዝቦቿ ለሰንደቅ ዓላማቸው ክብር በአንድነት የሚታገሉባት አገር በመሆኗ ነው፤ አሁን ላይ የሚስተዋለውን አክራሪ ብሔርተኝነትና ጎጠኝነትን ወደ ጎን በመተው፣ ቅድመ አያቶች የሰሩትን ታሪክ በማወቅ ወቅታዊ ፈተናዎችን በጥበብና በእውቀት ማለፍ ይገባል።

በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የፋርማሲ ትምህርት ክፍል ተማሪና የተማሪዎች ሕብረት ፕሬዚደንት የሆነው ወጣት ያሬድ ላቀው እንደሚለው ቤተሰቦቼ ስለ አድዋ ብዙ ነገሮችን ነግረውኛል እኔም ከአንደኛ ደረጃ ትምህርቴ ጀምሮ ዓድዋ የአንድ ብሔር ወይም ጎሳ ድል ሳይሆን፤ የመላው ኢትዮጵያዊ አኩሪ የድል ታሪክ መሆኑን ተምሬያለሁ ይላል።

እንደ ወጣት ያሬድ ገለጻ፤ ኢትዮጵያውያን ለነጭ አንገዛም ብለው በሌላቸው መሳሪያና ቴክኖሎጂ ከዳር እስከዳር ያላቸውን ስንቅና ትጥቅ በመያዝ ታላቁን ፋሽስት ሳያስበው ድል የነሱበት አኩሪ ታሪካችን በመሆኑ እኔም በዚህ ስሜት ውስጥ በመሆን የማከብረው ታላቅ የድል በዓል ነው።

ድልን እንደ አገር ስናገዝፍና ስናከብር ነው ወደሌሎች ድሎች የምናመራው የሚለው ወጣት ያሬድ በተለይም ዓድዋ ከድልነትም ባሻገር የእኛነታችን መገለጫ በመሆኑ አከባበሩም አገራዊ መልክና ቅርጽ ቢኖረው መልካም ስለመሆኑ ያብራራል።

አሁን ባለውና በምናየው ሁኔታ ወጣቶች ዓድዋን ይደግማሉ ማለት ከባድ ነው። ነገር ግን ስራዎች ከተሰሩ ወጣቶች ስለ አገራቸውና ስለታሪካቸው እንዲያውቁ ከተደረገ ወጣቱ ነገን በተሻለ መንገድ አያስብም ወይም ተስፋ ይቆርጣል ማለት እንዳልሆነም በመናገር፤ ነገር ግን እንደ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ሁሉ ሌሎች ከፍተኛ የትምህርተ ተቋማት ታሪክ ላይ ስራዎችን መስራት እንደሚጠበቅባቸው ብሏል።

ሌላው አገር በጣም ትንሽ የሆነ ታሪኩን በትምህርት በጥበብ ስራ ብቻ በተገኘው ነገር በሙሉ በማጉላትና ደጋግሞ በማውራት የዓለም ሕዝብ ጆሮና አይን ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል። በአንጻሩ እኛ ደግሞ ይህንን የሚያክል የድል ታሪክ እያለን እንኳን ሌላውን ለማሳወቅ ለራሳችንም ያወቅነው በጣም ጥቂቱን ነው። በመሆኑም የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ እንደ አገር ዓድዋ በትምህርት ስርዓት ውስጥ ራሱን ችሎ የሚገባበትና ከታችኛው የክፍል ደረጃ ጀምሮ ሕጻናት እየተማሩት እያወቁት እየኮሩበት እሱን ምርኩዝ አድርገው በተሰማሩበት መስክ ታሪክ እየሰሩ እንዲሄዱ ማገዝ ይገባል በማለት አስረድቷል።

"......ወጣቱ ታሪክን የሚጠላ ወይንም ደግሞ የአባት የእናቶቹ ታሪክ እሱን የማይመለከተው ሆኖ አይደለም ይልቁንም ታሪኩ ላይ ትኩረት እንዳያደርግ ኑሮ አልተመቸውም። የሚፈልገውን ነገር አያገኝም። በዚህ ምክንያት ደግሞ ቀዳዳውን ደፍነው አገራዊ ፍቅሩንና አንድነቱን የሚሸረሽሩበት ብዙ ናቸው፤ በመሆኑም ወጣቶች በተለይም ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ላይ ያሉ ዛሬን ሳይሆን ራቅ አድርገው እያሰቡ እያመዛዘኑ ሁሉንም በልኩ ማስኬድ አለባቸው"ሲልም ይገልጻል።

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ክፍል ተማሪና የተማሪዎች ሕብረት ዲሲፕሊንና መልካም አስተዳደር ዘርፍ ተጠሪ የሆነው ወጣት ረመዳን ኑርጌታ በበኩሉ እንደተናገረው፤ ዓድዋ አይቻልምን ወደ ይቻላል የቀየረ ነው። በዓሉን ማክበር ስናስብም ይህንን መለስ ብለን ማሰብና መገንዘብ ይገባናል።

ጣሊያኖች ለወረራ ሲመጡ ያሰቡትና ሆኖ ያገኙት ነገር ፍጹም የተለያየ ነበር፤ በቀላሉ ቅኝ ሊገዙንም እንደሚችሉ እርግጠኞች ነበሩ። ነገር ግን በወቅቱ የነበሩት እናት አባቶቻችን እንዲሁም አያቶቻችን ምንም እንኳን ያልተማሩ ዘመናዊ መሳሪያም ያልታጠቁ ቢሆኑም በገባቸው ልክ በአንድነትና በሕብረት በነቂስ ተመው እንኳን ለአገራቸው ለመላው ዓለም የሚያስደምም አንጸባራቂ ታሪክ ሰርተዋል።

ዓድዋ ከዛሬ 128 ዓመት በፊት አልፏል። ያንን አንጸባራቂ ድል መድገም ካለብን ግን አመቺው ጊዜ አሁን ነው የሚለው ወጣት ረመዳን በአገራችን እዚህና እዚያ እየሆነ ያለው ነገር ሁላችንም የምናውቀውና የምንገነዘበው ነው። በመሆኑም እነዚህን አለመግባባቶቻችንን በምክንያታዊነት ለአገር ክብርና አንድነት ቅድሚያ ሰጥተን ማየት ይገባናል።

ወጣቱ ትላንት ሳይማሩ በሕብረታቸውና በአንድነታቸው ጠላትን ያሳፈሩ የአባቶቹን ገድል በመከተል ዛሬም ለአገሩ ክብርና አንድነት መጠበቅ የበኩሉን መወጣት ይገባዋል።

".....አገር ላይ ጦርነት ሲኖር ሄዶ የሚዋጋው ወጣቱ ነው። እንዲሁም በቤቱ ቁጭ ብሎ በማኅበራዊ ሚዲያው የጥላቻ ንግግሮችን እየዘራ የሚያፋጀው ወጣቱ ነው፤ በመሆኑም የሚያደርገው ነገር መጨረሻው ምንድን ነው? ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለውን ማየትና ዛሬ ካለችን አገር ነገ እንድትሆንልን ከምንመኛት ኢትዮጵያችን አንጻር ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል የሚለውን መመዘን ይገባል"ብሏል።

ዛሬ ጣሊያን አልያም ሌላ የነጭ ወራሪ መጥቶብን አይደለም ዓድዋን የምንደግመው ይልቁንም እግር ተወርች አስሮን ባለው ድህነት። ብሔርተኝነት። ጎጠኝነት ላይ በመዝመት ዓድዋን በእያንዳንዳችን ዘንድ መድገም ይገባል በማለት ወጣት ረመዳን ያስረዳል።

ሁላችንም አሁን ባለው ስርዓት ላይ የማይመቹን ነገሮች ሊኖሩ፣ ልንከፋም እንችላለን። ነገር ግን ያ ሁሉ ነገር ከኢትዮጵያችን በታች መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። በባሕል በሀይማኖት በአስተሳሰብና አመለካከት የተለያየን ብንሆንም ሁላችንም መጠለያችን አገራችን ናት። በሌላ በኩል ደግሞ እምነታችንንም አመለካከታችንንም ለማራመድ አገር ያስፈልገናልና ይህንን መጠበቅ ከወጣቱ የሚጠበቅ ኃላፊነት ስለመሆኑ አስረድቷል።

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ክፍል ተማሪው ወጣት እንዳልካቸው ተስፋዬም ትላንት አባቶቻችን በሰሩልን አኩሪ ታሪክ ቀና ብለን ሄደናል። አሁንም በየዓመቱ ቀኑን እንዘክረዋለን፤ ይህ በጣም መልካም ነገር ነው። ነገር ግን እኛም ነገ ልጆቻችን የሚዘክሩት ታሪክ ልንሰራ ይገባል ይላል።

እንደ ወጣት እንዳልካቸው ገለጻ፤ ወጣቱ ብዙ የሚጠበቅበት ሚና አለ ለምሳሌ ገበሬ ክረምት ላይ ለፍቶ የዘራውን ነው በበጋ የሚሰበስበው፤ እኛም ዛሬ የሰራነው በጎም ሆነ መጥፎ ነገር ነገ እንደሚጠብቀን አስበን ቢያንስ የማናፍርበትን ታሪክ ሰርተን ለማለፍ መሞከር ይገባናል።

ዓድዋ መላው ሕዝብ አጥንቱን የከሰከሰበት ደሙን ያፈሰሰበት የነጻነት በዓላችን ነው፤ በዚህም ከቅኝ ግዛት ነጻ የሆነች አገርን ሊያስረክቡን ችለዋል፤ እኛ ደግሞ ለቀጣዩ ትውልድ ጥሩ ታሪክን ለማውረስ ዛሬ ላይ በተሰማራንበት መስክ ሁሉ ተግተን መስራት ይጠበቅብናል እንደ ወጣት እንዳልካቸው ገለጻ።

ብዙ የሚያራርቁን ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን በሚያመሳስሉን ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል እንደዛ ካደረግን አገራችን የትላንት ገናናነቷ ላይ የማትመለስበት ምክንያት የለም ይላል።

አዎ ዓድዋ የእኛ ብቻ ሳይሆን፤ የመላው ዓለም ድል የይቻላል መንፈስን ያመጣ ታላቅ በዓል ነው። እኛም ዛሬ የዓድዋ ልጆች ነን ብለን በየአካባቢው በትንሽ በትልቁ መራራቅና መቃረናችንን ትተን ልዩነቶቻችንን በጠረጴዛ ዙሪያ ፈተን ነገን ብሩህ ለማድረግ የራሳችንንም ታሪክ ለመጻፍ ዛሬ መነሳት አለብን።

# አበረታች ውጤት እያስገኘ ያለው የወላይታ ዞን- የማዕድን ልማት

**ማህሌት አብዱል**

በደቡብ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ዞኖች መካከል አንዱ የሆነውና ከአዲስ አበባ 300 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው ወላይታ ዞን በማራኪና ምቹ ስነ-ምሕዳሩ፣ ቱባ ባኅልና ስራ ወዳድ በሆነው ሕዝቡ ይታወቃል፡፡ በተለይም በዞኑ ያሉት በርካታ ወንዞችና ጅረቶች የአካባቢው መለያ ሆነው ይጠራሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር እንደግልገል ጊቤ ሶስት የኃይል ማመንጫ የመሳሰሉ ትላልቅ ሃገራዊ ፕሮጀክቶች የሚገኙበት ዞን ነው፡፡ ይኸው ዞን አሁን አሁን ደግሞ በተለያዩ ማዕድናት ሃብት ልማትም እየታወቀ ሲሆን በዋናነት ደግሞ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሆነው የድንጋይ ከሰል በስፋት በዞኑ መገኘቱን ተከትሎ ጥቂት የማይባሉ ባለሃብቶች የማዕድን ልማት ጥያቄ እያቀረቡ ስለመሆናቸው ከዞኑ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

የወላይታ ዞን ውሃ መስኖና ማዕድን ልማት መመሪያ ኃላፊ መሰረት በቀለ (ዶ/ር) ለአዲስ ዘመን እንደተናገሩት፤ ዞኑ በበርካታ የማዕድን ሃብት የታደለ ቢሆንም እስካሁን ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን አልተቻለም፡፡ ለዚህ ደግሞ በዋናነት በማኅበረሰቡ ዘንድ ከዚህ ቀደም ስለማዕድን በነበረው ዝቅተኛ ግንዛቤ የተነሳ ሃብቱ ለሃገርም ሆነ ለሕዝብ ጥቅም ላይ ሳይውል ቆይቷል፡፡ ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ግን እንደሀገር ለማዕድን ልማት ዘርፍ ልዩ ትኩረት መሰጠቱን ተከትሎ የዞኑም አስተዳደር ያለውን እምቅ የተፈጥሮ ሃብት ወደ ልማት ለማስገባት ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በዋናነትም በዞኑ ያሉትን የማዕድን አይነቶች እንዲሁም መጠናቸውን በውል ለመለየት ያስቻለው ዘንድ ከሐዋሳና ከወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄዱን ያስታውሳሉ፡፡ በተጠናው ጥናት መሰረትም እንደ ድንጋይ ከሰል፤ ካኦሊን፤ ኦፓልና ኮርቲዝ የመሳሰሉ ለኢንዱስትሪ ልማት እንዲሁም ለጌጣጌጥ ሥራ የሚያገለግሉ ማዕድናት በስፋት መኖራቸውን ያመለክታሉ፡፡ ከእነዚህ የማዕድን ሃብቶች መካከልም ለሲሚንቶና ለተለያዩ ኢንዱስትሪ ዋነኛ ግብዓት የሆነው የድንጋይ ከሰል በዞኑ አራት ወረዳዎች በስፋት መኖሩ እንደታወቀ ይጠቁማሉ። ‹‹በተጨማሪም ለጂኦተርማል የሚያገለግሉ የተፈጥሮ ማዕድናትን የያዘ ሃብት አለ፤ በተወሰነ መልኩ ደግሞ ንኬል፣ ዚንክ በተጨማሪ ጥናት የሚፈልጉ የማዕድን ዘርፎች ናቸው›› ሲሉም ያስረዳሉ፡፡

በመቀጠልም ማዕድኑ ስለመኖሩ ከባለድርሻ አካላት ጋር በማዕድኑና በልማቱ ዙሪያ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መሰራቱን ተከትሎ በርካታ ባለሃብቶችና ግለሰቦች ለማልማት ጥያቄ ማቅረባቸውንና የሥራ ፍቃድ መውሰዳቸውን መምሪያ ኃላፊው ይናገራሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ሶስት የሚሆኑት ኩባንያዎች ማምረትና ወደ ገበያ ማቅረብ መጀመራቸውን ያመለክታሉ። ይሁንና አብዛኞቹ ባለሃብቶች ፈቃድ ወስደው፤ የአዋጭነት ጥናት አስጠንተው ለማምረት በዝግጅት ላይ ስለመሆናቸው ነው ያብራሩት፡፡

‹‹ዞኑ አሰራርና መመሪያውን ተከትሎ የሚመጡ ባለሃብቶች ምቹ ምኅዳር በመፍጠርና አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ወደ ልማት እንዲገቡ እያደረገ ነው›› የሚሉት መምሪያ ኃላፊው፤ ፍቃድ ከወሰዱት ባለሃብቶች መካከል በብዛት ኦፓል፤ ካኦሊን፤ ድንጋይ ከሰል ለማምረት ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት በዞኑ በሚገኙ አራት ወረዳዎች ውስጥ ከ50 በላይ የሚሆኑ አልሚዎች በድንጋይ ከሰል ልማት ተሰማርተው እንደሚገኙ ገልጧል፡፡ እንዲሁም በኦፓል አራት፤ በካኦሊን


መሰረት በቀለ (ዶ/ር)

ደግሞ ሁለት የሚሆኑ ድርጅቶች ወደ ልማት መግባታቸውን ይጠቁማሉ፡፡

እንደ መምሪያ ኃላፊው ማብራሪያ፤ በአሁኑ ወቅት በዞኑ በሁሉም አካባቢዎች የሚገኙ የማዕድን ሃብቶችን ለማልማት በግላቸው የአዋጭነት ጥናት እያካሄዱ ያሉ፤ በቀጥታ ወደ ልማት ለመግባትም ዝግጅት እያደረጉ ያሉት ጥቂት የማይባሉ ናቸው። በዚህ ረገድም ዞኑ መመሪያና ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት አልሚዎችን የሚያበረታቱ አሰራሮችን ዘርግቷል፤ በመሆኑም የወላይታ ዞን በማዕድን ልማት ዘርፍ ምቹ መደላደል በመፍጠር ተጨማሪ አልሚዎች እንዲመጡ በመጋበዝ ላይ ይገኛል፡፡

የዞኑ አስተዳደር ከዩኒቨርሲቲና ምርምር ተቋማት ጋር በመቀናጀት ያጠናው ጥናት ላይ ተመስርቶ በአግባቡ የተሰነዱ መረጃዎችን ማዘጋጀቱን መምሪያ ኃላፊው ይናገራሉ፡፡ ‹‹ነገር ግን ያንን ሰነድ መሰረት አድርጎ ወደ ሥራ ከመግባት አንፃር ጥቂት የማይባለው ባለሃብት ዘርፉ አዲስ በመሆኑ ምክንያት ቶሎ ደፍሮ ወደ ልማት መግባት ይፈራል›› ይላሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ባለሃብቶቹ ዘርፉ ‹‹አዋጭ ላይሆን ይችላል›› የሚል ስጋት ያለባቸው እንደሆነና ስጋት ያደረባቸው መሆኑን ያስረዳሉ። ይህንን የአመለካከት ችግር መፍታት ያስችል ዘንድም በተለያዩ ጊዜያት የግንዛቤ ማሥጨበጫ ሥራ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣይም በቂ መረጃ በመስጠት ባለሃብቱን የማበረታታት ሥራ ይሰራልም ባይ ናቸው፡፡

እንደመምሪያ ኃላፊው ማብራሪያ፤ እንደሃገርም ቢሆን ካለው እምቅ የማዕድን ሃብት አኳያ የልማት ሥራው የሚገባውን ያህል ተካሂዷል ተብሎ አይታመንም፡፡ ምክንያቱም ደግሞ እንደሃገርም ሆነ እንደዞን ማዕድንን በማልማት ለኢኮኖሚው ዋነኛ የጀርባ አጥንት እንዲሆን በማድረግ ረገድ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ ነው፡፡ ዘርፉ እስካሁንም ብዙ ያልተሰራበትና የሚቀር በመሆኑ ነው፡፡ በተለይም ለኢንዱስትሪው ዋነኛ ግብዓት የሆኑ ድንጋይ ከሰል ማዕድናት የተወሰነ ኢንቨስትመንት የሚፈልጉ በመሆናቸውና አምራቹም ቶሎ ገቢ የሚያገኝበትን አነስተኛ ዘርፍ ተመራጭ ማድረጉ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ያም ቢሆን ግን አሁን ላይ አልፎ አልፎ የሚታየው የልማት እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪ እንደሆነ ያነሳሉ፡፡ ‹‹በእኛ ዞን ድንጋይ ከሰል ብንወስድ ማዕድኑ መኖሩ ታውቆ ወደ ልማት ከተገባ አንድ ዓመት እንኳን አይሞላም፡፡ አሁን ላይ በርካታ ኩባንያዎች ፈቃድ ወስደው እየሰሩ ይገኛሉ›› ይላሉ፡፡ በተጓዳኝም ባለሃብቱ ማዕድን በሚለማበት ቦታ መንገድ ሥራና መሰል የመሰረተ

> **በተጨማሪም ለወጣቶች የስራ እድል ከመፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማምጣት ረገድ የላቀ ሚና አለው፡፡ በመሆኑም ዘርፉን በመደገፍ ወደ ተሻለ የማምረት አቅም ማስገባት የሁሉም ባለድርሻ አካላት የቤት ሥራ ነው**

ልማት ዝርጋታ ላይ የየራሳቸውን ድጋፍ እያደረጉ ስለመሆኑ ይጠቅሳሉ፡፡ ‹‹ሆኖም ገና በጅማሬ ደረጃ ያለ እንጂ ብዙ የተሰራበት አይደለም›› ሲሉም አክለዋል፡፡

በዞኑ በማዕድን ዘርፍ ፍቃድ ወስደው የሚሰሩትም ቢሆኑ እያለሙ ያሉት በቀላሉ ተደራሽ በሆነበት ሥፍራ እንጂ ምቹ ባልሆኑና ርቀት ባላቸው ሥፍራዎች ደፍረው የማይገቡ መሆኑን የመመሪያ ኃላፊው ሲያስረዱ፤ ‹‹በእርግጥ በሚያወጡት ልክ ለዞኑ ገቢ እያስገቡ ነው ያሉት፤ እነሱ ከጀመሩ በኋላ የወረዳዎች ገቢ የጨመረበት ሁኔታም አይተናል፡፡ ሌሎች ፍቃድ የወሰዱ አካላት ደግሞ ወደ ማምረት ሲገቡ ገቢ ከመጨመር የራሱ በጎ ተፅዕኖ ይኖራል›› በማለትም ያብራራሉ። ለአብነትም የተቀናጀ የማዕድን ሃብት ቁጥጥር እና እንክብካቤ ሥራ በመስራት ከዘርፉ ስምንት ሚሊዮን ብር ገቢ የተሰበሰበ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ ይህም በራሱ ለቀጣይ ሥራ የሚያበረታታ መሆኑን ነው ያስገነዘቡት፡፡

በሌላ በኩልም የአካባቢው ወጣቶች ቀጥሮ የማሰራቱ ባሕል እየጎለበተ መምጣቱን ጠቅሰው፤ እንዲሁም በሁለተኛው ሩብ ዓመት በማዕድን ልማት ዘርፍ ለአምስት ሺ ወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ አምስት ሺ 350 ወጣቶች የሥራ እድሉ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ነው ያመለከቱት፡፡ ወጣቶቹ በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን እየደገፉ መሆኑ አበረታች እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ለልማት በሚገቡ ኩባንያዎች አማካኝነት ወጣቶቹ የልምድ ልውውጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ መልካም አጋጣሚ የፈጠረ መሆኑን ነው የመምሪያ ኃላፊው ያስገነዘቡት፡፡

እንደሳቸው ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ሃብት ጥቅም ላይ ማዋሏ እንደሃገር የውጭ ምንዛሪ ክምችታችንን ከማሳደግ አንፃር የላቀ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ በተለይም ከዚህ ቀደም ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ይገቡ የነበሩ እንደ ድንጋይ ከሰል አይነት የኢንዱስትሪው ዋነኛ ግብዓት የሆኑ ማዕድናት በሃገር ውስጥ ማምረት መቻሉ ጥቅሙ ዘርፈ ብዙ ነው። በዋናነትም የውጭ ምንዛሪውን በመታደግ ለኢኮኖሚው እድገት አወንታዊ ሚና ይጫወታል፡፡ በተጨማሪም ለወጣቶች የስራ እድል ከመፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማምጣት ረገድ የላቀ ሚና አለው፡፡ በመሆኑም ዘርፉን በመደገፍ ወደ ተሻለ የማምረት አቅም ማስገባት የሁሉም ባለድርሻ አካላት የቤት ሥራ ነው፡፡

ከዚሁ በተጓዳኝ በሕገወጥ መንገድ የሚደረገውን ማዕድን የማውጣትም ሆነ የመሸጥ ተግባር የመከላከሉ ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ መምሪያ ኃላፊው ይናገራሉ። ‹‹አሁን ላይ በሕገወጥ መንገድ የሚደረግ ማዕድን የማውጣት ሥራ ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት አልተቻለም፡፡ ይሁንና ከኅብረተሰቡ ጥቆማ ተነስተን ጠንካራ ክትትል እያደረግን ነው ያለነው፤ ግን ደግሞ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ ጥረት ይጠይቃል›› ይላሉ፡፡

ዞኑ ከዚሁ ጎን ለጎን ማዕድን ካወጡ በኋላ ቦታን ሳያስተካክሉ የሚወጡ ተቋማትን ለማየት መሞከሩን ያስረዳሉ፡፡ ማዕድን ለማውጣት አካባቢውን አላግባብ ቆፍሮ የሚተው አካላትን ተጠያቂ ለማድረግ እየሰሩ ስለመሆኑም ያመለክታሉ፡፡ ‹‹ምክንያቱም ደግሞ ይህ ተግባር ኅብረተሰብንም ሆነ ሃገርን ሊጎዳ የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ማዕድን ለማውጣት የቆፈሩበትን ወይም ያለሙበትን አካባቢ ስነ-ምህዳር የመጠበቅና እንደነበረ የመመለስ፣ የመንከባከብና የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው›› ሲሉም ያስገነዝባሉ፡፡ በተጨማሪም በውላቸው መሰረት ችግኝ የመትከል ስራ እንዲሰሩ የሚገደዱበት ሁኔታ መኖሩን ነው የተናገሩት፡፡

የዞን አስተዳደሩ ባሉት የማዕድን ሃብትና አቅም ልክ ለማልማት የሚመጡትን ኩባንያዎች ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን መምሪያ ኃላፊው ይናገራሉ። በዋናነትም ከማልማት በዘለለ ለወጣቶች ሥራ እድል በመፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ለራሱም እየተጠቀመ ማኅበረሰቡንም ለመጥቀም የሚፈልግ ማንኛውም አካል አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ የሚደረግለት መሆኑን ነው ያስገነዘቡት፡፡

በዞኑ ያለውን የማዕድን ሃብት ልማት በአይነትና በመጠን በማስፋት፤ ለሃገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ማደግና ለሀገር ኢኮኖሚ መበልፀግ ጉልህ አበርክቶ ይኖረው ዘንድም ሁሉም ባለድርሻ አካል የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል! የሚለው ደግሞ የዛሬው የዝግጅት ክፍሉ መልዕክት ነው፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## እንባ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

የትም ቦታ ምንም ነው። ሞልቶ ከፈሰሰ እልፍ ዘመናት ተቆጥረዋል። ልብ የሚወደውን ያክል መጥላትም እንደሚችል ቆይቶ ነው የገባው። አንዳንድ እድሎች አሉ፣ አንዳንድ ቀኖች አሉ፣ አንዳንድ አጋጣሚዎች አሉ የሚደገሙ መስለው ከታሪክ የሚሰወሩ። ስንስቅ..ስቀን ስንሰነብት ያሳቁንን ልቦች፣ ያሳቁንን ነፍሶች እንረሳለን። በደረቅ ፊት ላይ፣ በደብዛዛ ገጽ ላይ ሳቅን የዘሩልንን ጺጋዎቻችንን እንዘነጋለን።

አሁን ሌላ ነው..ሩታን እያሰበ የሚኖር። አሁን ሌላ ነው ከሩታ ጋር የሆኑትን፣ ያደረጉትን፣ ያወሩትን እያሰበ የሚኖር። እንደ እሷ ደስታን የሰጠችው፣ እንደ እሷ ግፍ የሰራባት ሴት የለችም። በመውደዷ ተማምኖ፣ በፍቅሯ ታብዮ በሴትነቷ ላይ እንደፈለገ ሲሆን ነበር። ብዙ ጊዜ አስቀይሟት ታርቃዋለች። ብዙ ጊዜ በድሏት ይቅርታ ብለዋለች። ብዙ ጊዜ የማይሆን ነገር ሲያደርግ በመተው አልፈዋለች። ነፍሱ ከስህተት የማትማር..አንድ አይነት ስህተትን ስትደጋግም የምትኖር ነበረች። አንድ ቀን ግን ሌላ ሆነችበት..አንድ ቀን ግን ከሚያውቃት ርቃና መጥቃ አገኛት። ያን ቀን፣ ያን ሴትነቷን አይረሳውም..

እያጨሰ ወደተቀመጠበት ቦታ እስከዛሬ ባልተራመደችው የዝግታ ርምጃ ተራምዳ አጠገቡ ቆመች። ከሚያቦነው ጭስ ጋር እየተጫወተ አላያትም ነበር። ሲያጨስ አያውቃትም። ሲጠጣ ትዝ አትለውም። እሱን መልካም ወንድ ለማድረግ የለፋችውን ልፋት ለሌላ ብትጠቀመው እሄኔ አለም ከሚያውቃቸው ስኬታማ ሴቶች ውስጥ አንዷን ሆና በቴሌቪዥን ያያት ነበር።

‹እኔ የሌለሁበት ዓለም ናፍቆህል አይደል? ጠየቀችው።

ዝም አላት። ሲያጨስና ሲጠጣ አያውቃትም..

‹አንድ ሴት የምትጎዳው ሴት ማለት ምን ማለት እንደሆነች የማያውቅ ወንድ ላይ ስትወድቅ ነው። የአንድ ወንድ የስልጣኔ ደረጃ የሚለካው ለሴት ልጅ ባለው ክብር ልክ ነው። ሴትን ማክበር ለእናትህ፣ ለእህትህ፣ ለልጅህ የምትከፍለው ውለታ ነው። እና ደግሞ የእኚህን ሶስት ነፍሶች ጎዳና መጥረግ ነው..ይሄን መቼም እንዳትረሳ።

ዞር ብሎ አያት..እጇ ላይ አነስተኛ ሻንጣ ይዛለች።

‹የት ልትሄጂ ነው? ጠየቃት። በአፍና በአፍንጫ በሚግተለተል ጭስ በታጀበ ቃላት።

‹አንተ የሌለህበት፣ ትዝታህ..ናፍቆትህ ከማይደርስበት..ወንድነትህ ከማይከተለኝ ሩቅ ቦታ› መለሰችለት።

ወፍራም እና ነፍናፋ ሳቅ ከጉሮሮው ወጣ። ‹እኔ የሌለሁበት የትም የለም..

‹እውነት ነው አንተ የሌለህበት የትም የለም ግን ነፍሴ አንተ የሌለህበትን አንድ ቦታ ፈልጋ አግኝታልኛለች..ወደዛ እየሄድኩ ነው። እርግጠኛ ነኝ መቼም አትደርስብኝም› አለችው።

‹አንድን ሰው ስትርቂው ይበልጥ እየተከተልሽው ነው..

‹ይበልጥም ግን ትርቀዋለህ..

‹አትልፊ..

‹እመነኝ አለፋም..

‹አንቺ ከልፋት ውጪ ለምንም አልተፈጠርሽም.. እንዲህ እንደ አሁኑ ሄደሽ መመለስሽን ረሳሽ እንዴ? ሲል በንቀት ጠየቃት።

‹እውነት ነው ሄጄ ተመልሼ አውቃለሁ። አጠገብህ ላልደርስ ምዬ ቃሌን አፍርሼ አውቃለሁ። ያኔ ግን የመለሰኝ ፍቅር ነው። ከውስጤ እውነት ይልቅ የአንተ ፍቅር በልጦ ከሸሸቴ መልሶኛል። አሁን ግን እመነኝ.. አልመለስም ልመለስ ብልም አይቻለኝም።

‹አንቺ ከኔ ውጪ ዓለም የሌለሽ ሴት ነሽ። እያፈቀርሽኝ እንድትኖሪ የተፈጠርሽ ነሽ።

‹ልብ ከማፍቀር እኩል መጥላትም እንደሚችል የማያውቅ ልብ ነው ያለህ። ለዚህ ልብህ የኔ ሄዶ መመለስ ጀግንነቱ ነበር። አሁን ግን ለዚህ ልብህ ዳግመኛ እድል አልሰጠውም። ዛሬ የምታየኝ ለመጨረሻ ጊዜ ነው። ፈልገህ ስታጣኝ፣ ጠብቀህኝ ስቀር ምን ያክል እንደራኩህ፣ ነፍሴም አንተ የሌለህበትን ስፍራ ፈልጋ እንደደረሰችበት ትረዳለህ። ለኔ የነፈከኝን ፍቅር፣ ክብር፣ መልካምነት ወደህይወትህ ለምትመጣው አዲስ ሴት እንድትሰጣት ደህና ሁን..›

ትታው ሄደች። ትታው ስትሄድ እንደምትመለስ እያወቀ ነበር። ትታው ስትሄድ እንደ እስከዛሬዋ እሱ የሌለበትን ቦታ ስታጣ ተመልሳ ወዳለበት እንደምትመለስ በማመን ነበር። ግን አልተመለሰችም ስምንት ዓመታት ተቆጠሩ።

ከስምንት ዓመት በኋላ ልብ ማፍቀር ብቻ አይደለም መቁረጥም እንደሚችል ተማረ። የሚያፈቅሩን ልቦች፣ መሄድ እየፈለጉ የሚያመነቱ እግሮች በፍቅር እግር ብረት ተይዘው እንደሆነ ተረዳ። የትም ቦታ ምንም ሆኖ ራሱን አገኘው። የቆመው በእሩታ ፍቅር እንደነበር ዛሬ ነው የገባው። በዓለም ስፍራ ሩታን ያልፈለገበት ቦታ የለም..አላገኛትም። እሱ የሌለበት ስፍራ ወዴት እንደሆነ አልደረሰበትም። ነፍሷ ፈልጋ ያገኘችላት እሱ የሌለበት፣ ትዝታው የማይደርስበት፣ ናፍቆቱ የመከነበት ስፍራ ከሃሳቡ ጠፋ። ሩታ ከእሱ ሌላ ህይወት እንደሌላት ነበር የሚያውቀው። እሷ የምሞተው ከአንተ የተለየሁ ቀን ነው ብላው ነበር። ታዲያ ከእሱ ውጪ እንዴት ህይወት እንዳገኘች አልገባውም። በዚህ ሃሳብ ብዙ ጊዜ ኖሯል።

ከስምንት ዓመት በኋላ አንድ ግሮሰሪ ውስጥ ነበር። ሩታን እያሰበ። ግሮሰሪው ባንኮኒ ላይ የመተኛት ያክል አዝምሟል..። አንድ ጊዜ ሲጋራውን፣ አንድ ጊዜ ደግሞ ብርጭቆውን ወደ አፉ እያለ ይለፋደዳል። አጠገቡ፣ ዙሪያው ወደዚያ ወደዚህ የሚሉ ሴቶች ይታዩታል። ከፊት ለፊቱ በሚያጨሰው የሲጋራ ጭስ ውስጥ ለዓመታት የጠፋችበትን ሴት አያት። ማመን አልቻለም..የሚያየውን እውነት ተጠራጠረ። ገና አልሰከረም..ትዝታውን ገርስሶ ለመጣል እንጂ ብዙም የመጠጣት አመል የለውም። የሚያጨሰውም ያቺን እንደ ተለኮሰ ላምባዲና የህይወቱን ጨለማ ገልጣ ሰው ያደረገችውን ነፍስ ለመርሳት ነው።

አፉ ላይ እየነደደ የሚጨሰውን ጭስ ወደ መተርኮሻው ጥሎ የፊትለፊቱን ሴት አያት። ራሷ ናት.. ማከዳ። የስቃዩ ማብቂያ ይቺ ሴት ናት። የሚጠይቃት እልፍ ጥያቄ አለው..

እየተንገዳገደ ወዳለችበት ተራመደ። አጠገቧ ደርሶ ማከዳ ሲል ጠራት..። አጠገቧ አብረዋት የተቀመጡ ሶስት ወንዶች በዓይናቸው ተከተሉት።

ዞራ አየችው። አላወቀችውም..

‹..አስታወሽኝ?

‹ይቅርታ አላስታወስኩህም..

በዚያ ሁኔታ ራሱን ማስተዋወቅ አልፈለገም.. ስላላወቀችው ደስ ብሎታል። ስላላስታወሰችው ስለ ሩታ እንደፈለገ ሊጠይቃት ይችላል። ሩታ በጣም የምወዳት ጓደኛዬ ናት ብላ አስተዋውቃው ነበር። ሊረሳት ያልቻለውም ቤት ከሩታ ጋር አብረው የተነሱት ፎቶ ስላለ ነው።

‹የሩታ ጓደኛ ነሽ አይደል? ሲል ጠየቃት።

በዝምታ ለረጅም ጊዜ አስተዋለችው።

‹እባክሽ ስለሩታ ንገሪኝ...ምንም እንዳትዋሽኝ! ሲል ተለማመናት።

የሆነ ነገር ትዝ ያላት መሰለ። ፊቷ ላይ የሆነ ትውስታ አንጃበበ። ‹አኬ..ቶማስ ነህ አይደል?

‹አዎ ነኝ..ሩታ የት ናት?

‹አዝናለሁ ቶማስ..ሩታ ካረፈች ሰባት ዓመት አልፏታል። ያኔ ካንተ እንደተለየች ነበር ራሷን ማጥፋቷን የሰማሁት› ብላው ተንሰቀሰቀች።

አጠገቧ አልቆመም ትቷት ሄደ። በመንገዱ በዝምታ ውስጥ ሲነፈርቅ ነበር። ለካ እኔ የሌለሁበት ዓለም ያ ኖሯል። ለካ ያን ቀን ዳግመኛ ወደአንተ አልመለስም፣ አንተም አትደርስብኝም ያለችው ወደ ሞት እየሄደች ነበር። በሩታ ፍቅር ዘመኑን ሙሉ ያለቅሳል። ዘመኑን ሙሉ ያቀረቅራል። ፍቅሯን፣ ደግነቷን ሲያስብ አይሆኑ ይሆናል።

# ዓለም አቀፍ



## ቻይና ትዳር የመሰረቱ ዜጎቿን ልሸልም ነው አለች

ቻይና ትዳር የመሰረቱ ዜጎቿን እንደምትሸልም ገለጸች። በቻይና አዲስ የሚወለዱ ሕፃናት ቁጥር በየዓመቱ እያሽቆለቆለ እንደሚገኝ ተገልጿል። ከሕንድ ቀጥሎ ሁለተኛዋ ባለ ግዙፍ ሕዝብ ቁጥር ባለቤት የሆነችው ቻይና በየዓመቱ የሚወለዱ ሕፃናት ቁጥር እየቀነሰባት ይገኛል።

ሀገሪቱ በየዓመቱ የሚወለዱ ሕፃናትን ቁጥር ለመጨመር የተለያዩ ማበረታቻዎችን በማድረግ ላይ ስትሆን፤ አሁን ደግሞ ዢያን የተሰኘችው ግዛት አዲስ ትዳር ለሚመሰርቱ የግዛቲቱ ነዋሪዎች ሽልማት አዘጋጅታለች።

እንደ ሮይተርስ ዘገባ ይህች ግዛት አዲስ ተጋቢዎች የጋብቻ ማስረጃቸውን ለሚያቀርቡ ዜጎች የሎተሪ እጣ ያዘጋጀች ሲሆን፤ አሸናፊዎች የ97 ሺህ ዶላር ሽልማት እና ሌሎች ስጦታዎችን አዲስ ተጋቢ ቻይናዊያንን ለማበረታታት እንደምትሰጥ ነው የተገለጸው።

በዢያን ግዛት ያሉ ተጋቢዎችን ከመጋቢት አንድ ጀምሮ እስከ ቀጣዩ ህዳር ወር ድረስ የሚያገቡ ጥንዶችን የተለያዩ ማበረታቻዎችን እንደሚሰጥ በዘገባው ላይ ተጠቅሷል። ቻይና ላለፉት ዓመታት ዜጎቿ ከአንድ ልጅ በላይ እንዳይኖራቸው የሚከለክል ሕግ የነበራት ሲሆን፤ ይህን ፖሊሲ ወደ ሁለት ልጅ ብታሻሽልም ዜጎቿ ልጅ የመውለድ ፍላጎታቸው እየቀነሰ መጥቷል ተብሏል።

በቻይና የተጋቢዎች ቁጥር መቀነስ፣ ልጅ ወልዶ ለማሳደግ የሚፈጀው ገንዘብ ከፍተኛ መሆን እና ከትዳር ውጪ ለሚወለዱ ሕፃናት መንግሥታዊ አገልግሎቶችን መከልከል አዲስ ለሚወለዱ ሕፃናት ቁጥር መቀነስ ዋነኛ ምክንያቶች እንደሆኑ ተገልጿል።

በእስያ በተለይም በጃፓን፣ ደቡብ ኮሪያ እና ቻይና አዲስ የሚወለዱ ሕፃናት ቁጥር በየዓመቱ እየቀነሰ ሲሆን፤ መንግሥታት ዜጎቻቸው ልጆች እንዲወልዱ በማበረታታት ላይ መሆናቸውን የአል ዐይን ዘገባ አመልክቷል።

## የቀድሞው የአውስትራሊያ ፖለቲከኛ ሰላይ ነበሩ ሲል የሀገሪቱ ደህንነት ኃላፊ ይፋ አደረጉ



አንድ የቀድሞ አውስትራሊያዊ ፖለቲከኛ ሀገሩን አሳልፎ ለውጭ ሰላይ “ሸጧል” ሲል የሀገሪቱ ደህንነት መሥሪያ ቤት ይፋ አደረገ። ይህን የገለጹት የደህንነት መሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ማይክ በርገስ፤ የቀድሞው የሕዝብ እንደራሴ መረጃ አሳልፈው ሰጥተዋል ብለዋል።

ሀገሩን ሸጧል የተባሉት የፓርላማ አባልም ሆነ መረጃ ተቀብላለች የተባለችው ሀገር ስም ይፋ አልሆነም። ይህ ዜና መውጣቱን ተከትሎ የአውስትራሊያ ዋና ከተማ እና የፖለቲካ ማዕከል የሆነችው ካንቤራ ተንጣለች። በርካቶች የሕዝብ እንደራሴው ስም ይፋ እንዲሆን እየጠየቁ ይገኛሉ።

ረቡዕ ዕለት በዋና ከተማዋ ዓመታዊ መግለጫ እየሰጡ የነበሩት የአውስትራሊያ ፀጥታ እና ደህንነት መሥሪያ ቤት ኃላፊ “ኤ ቲም” የተሰኘው ቡድን አውስትራሊያን “ቁጥር አንድ ዒላማ አድርጎ” ሲንቀሳቀስ ነበር ብለዋል።“ሰላዮቹ እንደ አማካሪ፣ የመንግሥት ባለሥልጣን፣ ምሑራን፣ አጥኚዎች አሊያም ደግሞ ከአንድ ልብ-ወለዳዊ ኩባንያ እንደመጡ አስመስለው ነው ሲንቀሳቀሱ የቆዩ” ብለዋል ኃላፊው።

ተማሪዎች፣ ምሑራን፣ ፖለቲከኞች፣ ነጋዴዎች፣ የፀጥታ ሰዎች፣ የመንግሥት ሠራተኞችን እና ሌሎችን በርካታ ሰዎች ዒላማ አድርገው ብር በመስጠት መረጃ ሲሰበስቡ ነበር ተብሏል። ስለ ንግድ፣ ፖለቲካ፣ የውጭ ጉዳይ እና የመከላከያ ፖሊሲ የመሳሰሉ መረጃዎችን ይሰበስቡ እንደነበር ኃላፊው ገልጸዋል።

አውስትራሊያ ከዩናይትድ ኪንግደም ጋር የፈረመችው የመከላከያ ስምምነት ዋነኛው ጉዳይ እንደነበር በርገስ ተናግረዋል። ነገር ግን በዚህ ቡድን ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ ሰዎች መካከል ጎልተው የወጡት የቀድሞው ፖለቲከኛ ሲሆኑ፤ “ስኬታማ በሆነ መልኩ ሰዎች ሲመለምሉ” ነበር ብለዋል።

እኒህ ፖለቲከኛ ለምን ያህል ጊዜ ሰላይ ሆነው ይሠሩ እንደነበር ኃላፊው አልተናገሩም።“ፖለቲከኛው ሀገራቸውን ሸጠዋል፣ ፓርቲያቸውን እና የቀድሞው የሥራ አጋሮቻቸውን ከደዋል፤ የውጭ ሀገርን ፍላጎት አስቀድመዋል” ብለዋል በርገስ። “በአንድ ወቅት እንዲያውም የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ለመመልመል ሙከራ ሲያደርጉ ነበር። ምንም እንኳ ይሄ ባይሳካላቸውም ሌላው ተሳክቶላቸዋል።”

ኃላፊው፤ እንደገለጹት፤ የቀድሞው ፖለቲከኛ አሁን ከቡድኑ ጋር አይሠሩም ብለው፣ የአውስትራሊያ ደህንነት መዋቅር ቡድኑን “በታትኖታል” አልፎም ሳያውቁ መረጃ እየሰጡ ያሉ ፖለቲከኞችም “እንዲያውቁት” ተደርጓል። የደህንነት መሥሪያ ቤቱ ባለፈው ዓመት ይህ ቡድን መበታተኑን የገለጹት ኃላፊው፤ አውስትራሊያውያን እንዲያውቁት እያደረግን ነው የሚል አስተያየት ሰጥተዋል።“አውስትራሊያውያን ሊያውቁት የሚገባው ነገር ስጋቱ የምር ነው፤ አሁን እየሆነ ያለ ነገር ነው፤ ከምናስበው በላይ ጥልቅ ነው።”

በርገስ በቅርቡ የቻይና ሰላዮች አውስትራሊያ ላይ ሊደቅኑት ስለሚችሉት ስጋት ተናግረው ነበር። ባለፈው ዓመት ደግሞ የሰላዮች “መንጋ” መበተናቸውን ከገለጹ በኋላ መገናኛ ብዙኃን ሰላዮች ሩሲያውያን ናቸው ብለዋል።

ምንም እንኳ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ፖለቲከኛው ስማቸው ይፋ አለመሆኑ ቅር ቢላቸውም የደህንነት ኃላፊውን ውሳኔ እናከብራለን ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

# ነፃ ሃሳብ

# ዋ ! ዓድዋ ...

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

የዓድዋ ድል ጀግኖች ሀገራቸው በቅኝ ገዥ እንዳትያዝ ለማድረግ ከጣልያን ጋር አንገት ለአንገት ተናንቀው የተዋደቁበትና የነጭን ወራሪ ድል ያደረጉበት ነው፡፡ በዚህም ጦርነት እናቶቻችን እና አባቶቻችን ደማቸውን አፍሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው በደማቅ ቀለም የኢትዮጵያን ታሪክ ለዓለም በሚያንፀባርቅ መልኩ ጽፈዋል፡፡

ከዓድዋ ጦርነት በፊት ግን ጣልያኖች በዶጋሊ፣ ሰገነይቲ፣ ሰንአፌ፣ አምባላጌ፣ መቀሌና ኩአቲት ከኢትዮጵያ ጋር ተዋግተው ተሸንፈው ነበር። የሰንአፌና ኩአቲት ጦርነት ድል የተመዘገበው በምኒሊክ ዘመን በራስ መንገሻ ዮሐንስና በራስ አሉላ ጦር ነው፡፡

ድሉ 128 ዓመት አስቆጥሯል፡፡ የዘንድሮው በዓል ልዩ የሚያደርገው ደግሞ እንደ ድሉ ሁሉ ዘመን ተሻጋሪ የሆነ የዓድዋ ድል መታሰቢያ በአዲስ አበባ መገንባቱና ባለፈው የካቲት 3 ቀን መመረቁ ነው። ይህን የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ለአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ የተሳተፉ መሪዎችና ተጋባዥ እንግዶች ጎብኝተውታል፡፡ በሙዚየሙ መደመማቸውንም ለመግናኛ ብዙኃን ሲገልጹ ተስተውሏል፡፡

በግሌም መሪዎቹና ሚኒስትሮቹ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ኅራ ማለታቸውን ስሰማ ጉራ ቢጤ ተሰምቶኛል፡፡ ደስም ብሎኛል፡፡ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድኅን ዋ! ያቺ .... ዓድዋ በሚል ከ52 ዓመት በፊት የተቀኘባትን ግጥም እንዳስታውስ አድርጎኛል።

« ዋ! ....
ዓድዋ ሩቅዋ
የዓለት ምሶሶ አድማስ ጥግዋ
ሰማይ ጠቀስ ጭጋግ ዳስዋ
ዓድዋ ....
ባንቺ ሕልውና
በትዝታሽ ብፅዕና
በመስዋዕት ክንድሽ ዜና
አበው ታደሙ እንደገና .... »

በነገራችን ላይ የካቲት 3 ቀን 2016 ዓ.ም. በይፋ የተመረቀው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ታላቅ ሀገራዊ ፋይዳ ያለው ነው፡፡ 128ኛው ዓድዋ በሚከበርበት ዘመን ይህን ዘመን ተሻጋሪ አስደማሚ ሙዚየም መሠራቱ ዓድዋ የበለጠ የሚያጎላ፣ ዜጎችን የሚያኮራ፣ ቱሪስቶችንና ጎብኚዎችን የሚጠራ ነው፡፡ እያጎጠጎጠ ያለው ጎጥ (ጎጠኝነት) የጥላቻና ሽኩቻ ትርክቶች አስወግደን ባንድነት እንድንቆም ግድ ይለናል፡፡ በመደመር እንጂ በመደናበር ጠላት ድህነትን ማስወገድ አይቻልም። እርስ በርስ መቃቃርና መናቆር ፋይዳ ሳይሆን ፍዳ እንዳያመጣብን ተገንዝበን ዓድዋን አስበን ከግጭት መራቁና እርቅ መፍጠሩ ይበጀናል፡፡

የታሪክ መዛግብት እንደሚያመለክቱት፤ ጣልያን ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ማንዣበብ የጀመረችው በዐፄ ዮሐንስ ዘመን ነው፡፡ የጣልያን ወታደሮች በእንግሊዝ አይዞህ ባይነት ግብፆችን ተከተው ምፅዋ የገቡት ጥር 28 ቀን 1878 ነበር፡፡

ወታደሮች በወቅቱ ጠረፍ እየወረሩ ስለነበር የመረብ ምላሽ ገዥ ራስ አሉላ ለኢጣልያው አዛዥ ለጄኔራል ካርሎ ዠኔ የያዘውን የኢትዮጵያን ምድር ለቆ እንዲሄድ ላኩበት፡፡ አለቅም ብሎ ገለፀላቸው፡፡ በኋላም በሰሐጢ መሽጎ ይጠባበቅ ከነበረው ማጀር በረቲ ውጊያ ገጥመው ድል አደረጉት፡፡ ቀጥሎም ሌተናል ኰሎኔል ክርስቶፎረስ ሦስት ክፍል የጦር ሠራዊት ይዞ 1879 በጥር 20ዎቹ መግቢያ ከምፅዋ 500 ገደማ ሠራዊት የተላከለት የኢጣልያ ጦር ዶጋሊ ላይ ገጥሞ፤ የአሉላ ጦር ከቦ ሁሉንም ዶጋመድ አደረገው፡፡

በጦርነቱ ጣልያን 23 የጦር መኮንኖችን ስታጣ 407 ደረጃ ያላቸው ወታደሮች ደግሞ እንደተገደሉባት ሰነዶች ያሳያሉ፡፡ በዚህም ጣልያን ሰዓቲን አስረክባ ወደ ቀይ ባሕር ጠረፍ ሸሸች፡፡ የዶጋሊ ድል በጣልያን ሲሰማ ከፍተኛ ደንጋጤና ሀዘን ፈጠረ፡፡ ወዲያው ሽንፈቱን እንዲመልሱ ታስቦ 20ሺ የጣልያን

**በሀገር ፍቅር ስሜት ይዋጋ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር በስልትና በቅንጅት ከጠላት ልቆ በመገኘቱ ብዙ ሰው ቢያልቅም እኩለ ቀን ላይ ጦርነቱ አከተመ**

ወታደሮች ምጽዋ እንዲሰበሰቡ ተደረገ፡፡

የጣልያን ወዳጅና የዐፄ ዮሐንስ የአጎት ልጅ የነበረው ፊታውራሪ ደበበ ከጣልያን ተጣልቶ ሰገነይቲ ሸፍቶ መሽጎ አስጨንቋቸው ነበረ፡፡ በነሐሴ 2 ቀን 1880 ዓ.ም ሰገነይቲ አምርተው ድንገተኛ ጥቃት ለመፈጸም በመዘጋጀት ላይ እንዳሉ ደበበ ከሁለት ቀን በፊት መምጣታቸውን ሰምቶ እንቅስቃሴያቸው ይከታተል ነበር፡፡ ለዚህም ሴት፣ ሽማግሌ ልጅ ከመንደሩ አስወጥቶ ጠበቃቸው፡፡ ተኩስ ከፍቶ ጦርነት ተካሄደ፡፡

በዚህም 5 የጣልያን የጦር መኰንኖችና 250 ወታደሮቻቸው ተገደሉ፡፡ ያልቆሰሉ ሸሽተው ምፅዋ ገቡ፡፡ ደበበ 470 ጠብመንጃ የታጠቁና 400 ጐራዴና ሳንጃ የታጠቁ ተዋጊዎች ነበሩት፡፡ ሰገነይቲ ከዶጋሊ ቀጥሎ ጣልያኖች የሽንፈትን ጽዋ የተጐነጩበት ነው፡፡

ጣልያኖች መረብን ተሻግረው ትግራይ አካባቢን የወረሩት በመስከረም1888 ነበር፡፡ንጉሡ ችግሩን ለመፍታት በዲፕሎማሲ ጥረት ሞክረው ጣልያኖች አሻፈረኝ ስላሉ፤ ከ100 ሺ ጦር ላይ ይዘው ከእቴጌይቱ ጋር ወደ ሰሜን ዘመቱ፡፡ በወቅቱ ሀገሪቱ መደበኛ ጦር አልነበራትም፤ በሰላም ጊዜ አርሶ አደርና አርብቶ አደር በግጭት ጊዜ ደግሞ ወታደር ሆኖ የሚያገለግል ሕዝብ ነበር፡፡

ዓድዋ ከአዲስ አበባ 1ሺ66 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ለጦርነቱ ዋና መነሻ የውጫሌ ውል ነበር፡፡ የውጫሌ ውል የተፈፀመው ከአዲስ አበባ በስተሰሜን 468 ኪሎ ሜትር ርቀት በምትገኘዋ ከአምባሰል ተራራ ግርጌ በውጫሌ ነበር፡፡

የውጫሌ ውል መፍረሱን ተከትሎ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን መውርር በጀመሩ ጊዜ ምኒሊክ ክተት አወጁ፡፡ “ወረኢሉ እንገናኝ” ሲሉ አስነገሩ፡፡

የዓድዋ ውጊያ መጀመሪያ በኅዳር 29 ቀን አምባላጌ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ራስ መኮንን ጣልያኖቹ ያሉበትን ቦታ በሰላም ለቀው እንዲወጡ በመደራደር ላይ ሳለ ፊታውራሪ ገበየሁ ሠራዊቱን የአምባላጌን አቀበት እየተዋጋ ወጥቶ ጣልያንን ድል አደረገ፡፡

በወቅቱ የጣሊያን ጦር አዛዥ ቶዚሊ ከሞቱት መካከል ሲሆን የቀረው የጣልያን ጦር ተበተነ፡፡ በወቅቱ ገበየሁ ድል በማድረጋቸው አዝማሪ እንዲህ ገጠመላቸው :-

**የንጉሥ ፊታውራሪ የጐራው ገበየሁ፣**
አላጌ በሩ ላይ ማልዶ ቢገጥማቸው፣
ለምሳም አልበቁት ቁርስ አደረጋቸው፡፡

በጥር ወር ከጣልያኖች ጋር የነበሩት የሐማሴኖቹ ራስ ስብሐትና ደጃች ሀጎስ ከኢትዮጵያ ጠላት ጋር ሆነን ሀገራችንን አንወጋም ብለው ከነባንዳቸው መጥተው ከንጉሡ ጋር ተቀላቀሉ፡፡ ምኒሊክ ጦሩን መርተው ዓድዋ ሲደርሱ፤ ጣልያኖች ከአዲግራትና እንጢቾ ምሽጋቸው ወጥተው ጦርነት የሚገጥሙበትን መጠባበቅ ጀመሩ፡፡

የካቲት 23 ቀን በማለዳ የጣልያን ጦር አዛዥ ጄኔራል ባራቴሪ ድንገተኛ አደጋ ለመጣል ጦሩን አንቀሳቀሰ፡፡ በሦስት መስመር ያጠቃ የነበረው የጣልያን ጦር እርምጃዎች ማቀናጀት ተሳነው፡፡ በአልቤርቶኒ የሚመራ ብርጌድ በተሳሳተ ካርታ ንባብ ከሁለቱ ብርጌዶች ተነጥሎ ለተባበረው የኢትዮጵያ ጦር ጥቃት ተዳረገ፡፡ አልቤርቶኒን ለማዳን የገሰገሰው የዳቦርሜዳ ጦርም መንገድ ስቶ በባዶ ሜዳ ቀረ፡፡

በሀገር ፍቅር ስሜት ይዋጋ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር በስልትና በቅንጅት ከጠላት ልቆ በመገኘቱ ብዙ ሰው ቢያልቅም እኩለ ቀን ላይ ጦርነቱ አከተመ፡፡ 10 ሺ የሚደርስ የጣልያንን ጦር ጨምሮ ጄነራል አርሞንዲና ዳቦር ሜዳ ተገደሉ፡፡ የጣልያን ቅኝ አገዛዝ ህልም ዓድዋ ላይ እልም አለ፡፡

በዓድዋ ጦርነቱ ከሞቱት መካከል ልዑል ዳምጠው፣ ደጃዝማች መሸሻ፣ ደጃች ሜጫ፣ ደጃች ገነሜ ይጠቀሳሉ፡፡ ፊታውራሪ ገበየሁ እና ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ፊታውራው ገበየሁ ከመሞታቸው በፊት

«**የዓድዋ ሥላሴን ጠላት አረከሰው
ገበየሁ በሞቴ ግባና ቀድሰው**» ተብሎ
ተገጥሞላቸዋል፡፡

በጦርነቱ ሲሞቱ ደግሞ እንዲህ ተገጠመላቸው፡-

«ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ
**መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ፣
አሻግሮ ገዳይ ፥ ዲብ አንተርሶ
የዳኛው አሽከር ፥ ባልቻ አባ ነፍሶ።** »

በዚህ ጦርነት ሊቀ መኳስ አባተ በያዙት መድፍ አነጣጥረው የጣልያኖችን መድፍ ባፉ አግብተው ሰባብረውት ስለነበር እንዲህ ተገጠመ«

**አባተ አባ ይትረፍ ነገረኛ አዋሻኪ ሰው
ይህን መድፍ ከዚያ መድፍ አቆራረጠው።
በሻ ጉድ አስ ጣልያን ወተወተ
ዐይነ ጥሩ ተኳሽ በዋለው (ባ ያለው) አባተ፡፡**

በዚህም በዐድዋ የነጭን ወራሪ ድል ያደረገችዋ ኢትዮጵያ ዝናዋ በዓለም ተሰማ፡፡ በቅኝ ግዛት ሥር የነበሩ ጥቁሮች ሁሉ እኛም ማሸነፍ እንችላለን የሚል ተስፋ ፈነጠቀላቸው፡፡ ይህም ለፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ መነሻ ሆነ፡፡ የኢትዮጵያ ስም በዓለም ላይ ናኘ። በአፍሪካውያን ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም በሚገኙ ጥቁሮችና ነፃነት ናፋቂዎች ዘንድ፡፡ ቅኝ ገዥዎቹ ነጮች ለኢትዮጵያ ክብርና ዕውቅና ሰጡ፡፡ በአፍሪካ የመጀመሪያ ኤምባሲዎቻቸውንም በአዲስ አበባ ከፈቱ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን መቀመጫውን አዲስ አበባ አድርጎ ሲከፈትም በዚህ አንፀባራቂ ድል ምክንያት መሆኑ እሙን ነው፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም በዐፄ ኃይለሥላሴ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከተማ ይፍሩ ሌሎች ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያኖችና ዲፕሎማቶች ጥረት መቀመጫው አዲስ አበባ ተደረገ፡፡ ይህም አዲስ አበባን ከኒውየርክና ጄኔቫ ቀጥላ ሦስተኛ ዓለም አቀፍ የዲፕሎማቲክ ከተማ ለመሆን አስችሏታል፡፡

ዓድዋ ከአዲስ አበባ ያለውን ርቀት አስበን ከደቡብ እና ከምሥራቅ የመጡ ጦሮች ስናሰላ እስከ 2ሺህ ኪሎ ሜትር የተጓዘ ጦር እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡ ለዚያው በእግርና በፈረስ አቀበቱን ቁልቀለቱን ጋራ ሸንተረሩን ዓድዋ የሄዱ ዜጎች ነበሩ፡፡ መደበኛ ጦር ያልነበራት ኢትዮጵያ በዓድዋ ተዋድቀው ታሪክ ያፃፉላት አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ነበሩ፡፡ በችግር ጊዜ ተጠርተው ከግብርናቸው ተነስተው የዘመቱ ዜጎች ዘመናዊ መሣሪያ ያልነበራቸው፤ ቢኖራቸውም አጠቃቀሙን የማያውቁ ነበሩ፡፡ እናም አብዛኛው ተዋጊ ጦርና ጎራዴ የታጠቀ ጋሻ የያዘ ከፊሉ እግረኛና ገሚስ ፈረሰኛ ነበር፡፡

ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ የኢትዮጵያ ታሪክ በሚል መጽሐፋቸው የዓድዋ ድልን የቅኝ ግዛት ማዕበልን የገታ፣ የቅኝ ገዥዎችን ቅስም የሰበረ ይሉታል፡፡ በዓድዋ ጦርነት ትረካው ለጣልያን ግልፅ ወገናዊነት የሚያሳየው ጆርጅ በርክሌ እንኳን « ከሰፊው የፖለቲካና ታሪክ ትንታኔ አኳያ የዓድዋ ጦርነት በአፍሪካ ምድር አዲስ ኃይል መነሳቱን የሚያበስር ይመስላል፡፡ የዚያች አህጉር ተወላጆች የማይናቅ ወታደራዊ ኃይል ሊሆኑ እንደሚችሉ ልናሰላስል ተገደናል፡፡ እንዲያውም አሁን ነገሩ አስቂኝ ቢመስልም፤ ይህ ሁኔታ (ማለትም ዐድዋ) ጨለማይቱ አህጉር በላይዋ ላይ ሥልጣኗን ባንሰራፋችው በአውሮጳ የምታደርገው አመፅ የመጀመሪያ ምዕራፍ ነውም ተብሏል » ሲሉ ጠቅሰዋል።

በዘመኑ የነበሩ ዜጎች የእምነትና የብሔር ልዩነታቸውን ወደ ጎን ትተው «መጀመሪያ መቀመጫዬን» እንዳለችው ዝንጀሮ መጀመሪያ ሀገሬን ብለው በአንድነት ተዋግተዋል፡፡ ተሽከርካሪም ሆነ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ በሌለበት በዚያን ወቅት በእግራቸው ዳገት ቁልቁለቱን እየሄዱ ዓድዋ ደርሰው ከጣልያን ወራሪ ጋር ተዋግተው ሀገራቸውን ከወራሪ ማዳን ችለዋል፡፡

የአሁኑ ትውልድ ከዓድዋ ድል መማር ያለበት የአንድነትን ጥቅም ነው፡፡ ስለሆነም ትውልዱ ከመገፋፋት እና ከማይጠቅም መጠላለፍ ወጥቶ አንድ በመሆን ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን የሚፈልጉትን ጠንካራ የሀገረ መንግስት የመገንባት ሂደት ውስጥ የራሱን አሻራ ሊያሳርፍ ይገባል ባይ ነኝ፡፡

# ስፖርት





# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከዓመታት በኋላ የስፖርት ውድድሩን ያካሂዳል

ብርሃን ፈይሳ

የተተኪ ስፖርተኛ ምንጭ ከሆኑ ስፍራዎች መካከል የትምህርት ተቋማት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚዘልቁ የስፖርት ውድድር መድረኮች በብሄራዊ ቡድን ደረጃ ሀገርን መወከል የቻሉ በርካታ ወጣቶችን ማፍራት እንደሚቻል ይታመናል፡፡ ይሁንና ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል የሚካሄደው ዓመታዊ ውድድር እየተቀዛቀዘ ሄዶ እስከ መቋረጥ ደርሷል፡፡

በርካታ ስፖርተኞችን በማፍራትና ደማቅ ፉክክሮችን በማስተናገድ ከሚታወቁ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል አንዱ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡ አንጋፋው የትምህርት ተቋም ከመማር ማስተማር ባለፈ በስፖርት ሳይንስ ትምህርት ክፍሉ በርካታ ባለሙያዎችን በተለያዩ ዘርፎች በማፍራት በኢትዮጵያ ስፖርት ጥናትና ምርምርን ጨምሮ በርካታ ተግባራት በማከናወን ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ ተማሪዎች በአካልና በአእምሮ ብቁ እንዲሆኑም ከትምህርታቸው ጎን ለጎን በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች በማሳተፍ ደማቅ ውድድሮችን እንደሚያከናውን ይታወሳል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ከተማሪዎቹ ውጪ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎቹን ለሌሎች ስፖርተኞች ልምምድ በመፍቀድም ምስጉን ነው፡፡ ይሁንና ለዓመታት ይህ ሁኔታ ተቋርጦ የስፖርት ሜዳዎቹም ጭር ብለው ከርመዋል፡፡

አሁን ግን በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ መሆኑን ተከትሎ ተቋርጠው የቆዩ የተለያዩ መርሀ ግብሮች እየተመለሱ ሲሆን፤ በተማሪዎች መካከል የሚካሄደው የስፖርት ውድድርና ፌስቲቫልም ከቀናት በኋላ በአዲስ መልክ የሚጀመር ይሆናል፡፡

ከየካቲት 29/2016 ዓ.ም አንስቶ ለ15 ቀናት ይዘልቃል



የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ሳሙኤል ክፍሌ (ዶ/ር)፤

የተባለው ይህ ውድድር በ5 የስፖርት ዓይነቶች ማለትም በፓራሊምፒክ፣ እግር ኳስ፣ አትሌቲክስ፣ ቅርጫት ኳስ እና ቮሊቦል ውድድሮችን እንዲሁም የተለያዩ ፌስቲቫሎችን ያከናወናል፡፡

በዩኒቨርሲቲው ስር ባሉት ኮሌጆች መካከል የሚከናወነው ውድድሩ በወንዶች እግር ኳስ 12 ኮሌጆች በአራት ምድብ ተከፍለው የሚጫወቱ ይሆናል፡፡ በሴቶች ደግሞ አራት ኮሌጆች የእግር ኳስ ውድድሩ ላይ ይሳተፋሉ፡፡ በአትሌቲክስ 10 የወንድና 6 የሴት ቡድኖች የሚካፈሉ ሲሆን፤ በቮሊቦል ደግሞ 9 የወንድ እና 3 የሴት ቡድኖች ተመዝግበዋል፡፡ በፓራሊምፒክ 3 የወንድና 2 የሴት ቡድኖች እንዲሁም 7 የቅርጫት ኳስ ቡድኖች ውድድሩን የሚያደምቁት ይሆናል፡፡ ውድድሮቹ የሚከናወንባቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ምቹ በሆነ ሁኔታ ተጠግነው መዘጋጀታቸውም ተገልጿል፡፡

ውድድሩን በሚመለከት ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ሳሙኤል ክፍሌ(ዶክተር)፤ መርሀ ግብሩ ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ መሆኑን ተከትሎ ከተደረጉ ለውጦች መካከል አንዱ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ትምህርት ቤቶች በኢትዮጵያ ስፖርት ተተኪ ስፖርተኞችን በማውጣት ያላቸው ሚና ይታወቃል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ባለፉት 73 ዓመታት የራሱን አበርክቶ አድርጓል፡፡ ባለፉት ዓመታት ሜዳዎች የስፖርት እንቅስቃሴ ስላልነበረባቸው አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ነበሩ ነገር ግን ከተለያዩ አጋር ተቋማት በተደረገው ድጋፍ ፌስቲቫሉ ተዘጋጅቷል፡፡

ተማሪዎች ሁለንተናዊ ስብዕናቸው አእምሯቸው፣ ጤናቸው እና የአካል ብቃታቸው የዳበረና የተሟላ ሁሉ አቀፍ ሆነው በቀጣይ የሀገር መሪዎች፣ ተመራማሪዎችና የተስተካከለ ስብዕና እንዲኖራቸው ስፖርት መሰረት በመሆኑ ይህ ፌስቲቫል ሊዘጋጅ እንደቻለም ተጠባባቂ ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል፡፡

በዚህ ዓመት በተወሰኑ ስፖርቶች ብቻ ውድድሮች የሚደረጉ ሲሆን፤ በቀጣይ ግን በየካምፓሶቹ ያሉ የስፖርት ሜዳቸውን በማስፋፋት፣ በመጠገንና ደረጃቸውን በማሻሻል ተማሪዎች በፌስቲቫል ብቻም ሳይሆን በስፖርት ተሳትፈው ጤናቸውን እንዲጠብቁ እንዲሁም ስፖርት የዩኒቨርሲቲው ባህል እንዲሆን እንሰራለን፡፡ ለዚህም ስፖርቱን የሚመሩት መንግሥታዊ ተቋማት እና የስፖርት ማህበራት አብረዋቸው እንዲሆኑም ጠይቀዋል፡፡

የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት በበኩላቸው፣ አንጋፋውና በኢትዮጵያ ታሪክ የማይሻር አሻራ ያለው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ወደቀደመ ከፍታው ለመመለስ በሚያደርገው ጉዞ ስፖርትን ማካተቱ የሚያስመሰግነው መሆኑን አንስተዋል፡፡

ስፖርት ከሚያድግባቸው ስፍራዎች ቀዳሚው ትምህርት ቤት ነው፤ በመሆኑም ሌሎች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም ከዚህ ትምህርት መውሰድ አለባቸው፡፡ የኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲም ንቁ፣ ተወዳዳሪና አሸናፊ ዜጋ መፍጠር አለበት የሚል አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ የከፍተኛ ተቋማት ስፖርት ፌስቲቫልም ለዚህ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። በመሆኑም የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር በመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል ይካሄድ የነበረው የስፖርት ውድድር በቀጣዩ ዓመት እንዲካሄድ በእቅድ መያዙንም አመላክተዋል፡፡